

PRODUCED BY #KALTUBE
POWERED BY MHgraphics

# ቃሬኛ

መንፈሳዊ መፅሔት

በ 7ሜ.ባ ብቻ
PDF ያውርዱ!
Online የገፃች
ኀበብ 21ሜ.ባ

በዚህ እትም
*********

**ቤተክርስቲያን ማን ናት?**
በነብይ መሳይ አለማየሁ

**ማህበራዊ ሚዲያና ክርስትና**
በዘሪሁን ግርማ

**እግዚአብሔር በህይወታችን ያለውን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን?**
በአቤኔዘር አለማየሁ

**መፅሐፍ-ቅዱስ ስለ ጅንጀና (Flirting) ምን ይላል?**
በአድነው ተመስገን

**ትንቢታዊ-ጋብቻ ምነው ትቢያ ሆነሳ?**
በቢንያም አዲሱ

እና ሌሎችም
*********


## 18 ጥያቄዎች
# ለህይወት መለሰ

ቃሬኛ


የመጀመርያ ዕትም

ቃልኛ መንፈሳዊ መፅሔት


# ማውጫ


መግቢያ
ገፅ-03




ቤተክርስቲያን ማን ናት?
በነብይ መሳይ አለማየሁ
ገፅ-04



ማህበራዊ ሚዲያና ክርስትና
በዘሪሁን ግርማ
ገፅ-09




እግዚአብሔር በህይወታችን ያለውን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን
በአቤኔዘር አለማየሁ
ገፅ-11



18ጥያቄዎች ለህይወት መለሰ
ገፅ-14



ነቢያትና አገልግሎታቸው ምንድነው?
በነብይ መሳይ አለማየሁ
ገፅ-19



መፅሐፍቅዱስ ስለ ጅንጀና (Flirting) ምን ይላል
በአድነው ተመስገን
ገፅ-24



ትንቢታዊ ጋብቻ ምነው ትብያ ሆነሳ?
በቢንያም አዲሱ
ገፅ-28

# መግቢያ

የክርስቶስ ሰላምና ፀጋ ይብዛላችሁ! እንኳን ወደ ቃልኛ ዲጂታል መንፈሳዊ መፅሔት የመጀመርያ ዕትም በሰላም መጣችሁ። ቃልኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ አምነው የዳኑ ቅዱሳንን ለማነፅ፣ለማፅናናት፣ ለማበረታታት እና ለማስተማር እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ ላላመኑ የዘላለም ህይወት ተስፋ የሆነውን የምስራች ወንጌልን ለማብሰር በቃልቲዩብ የቴሌግራም ቻናል የተዘጋጀ ልዩ ዲጂታል መፅሔት ነው። ቃልኛ ስሙን ከቃልቲዩብ የወረሰ ሲሆን በ ዩሐ 1÷14 መሰረት "ቃል" የሚለው ስያሜ ኢየሱስ ክርቶስን የሚወክል ነው። ቃልኛ በመፅሐፍ-ቅዱሳችን ስለ እግዚአብሔር እና የዘልአለም ህይወት በአዲስኪዳን የመጡት መገለጦች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደመሆኑ የአምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አስተምህሮዎች በመከተል 'የኢየሱስ ቋንቋ' የሚለውን ስያሜ ለመስጠት ቃልኛ ተብሎ ተሰይሟል። መፅሔታችን ላይ የሚገኙት የሁሉም መልዕክቶች መሰረትም በዚህ ላይ ያርፋል። መፅሔታችን ወጣቶች ላይ አተኩረው የሚሰሩ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተቀረፁ አምዶችን አካትቷል። አንባቢያኖቻችን በዚህ በኮሮና ወረርሽኝ ወቅት መፅሐፍቅዱስና መንፈሳዊ መፅሐፍትን እያነበባችሁ በፀሎትም እንትበረቱ እናሳስባለን። የመጀመርያ ዕትማችን እውን እንዲሆን በአምደኝነት በፁህፎቻችሁ እና በተለያየ ሀሳብ ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ለረዳችሁን በሙሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

መልካም ቆይታ ከቃልኛ ጋር!

CONTACT US
KALGNA DIGITAL MAGAZINE
EMAIL-SUPSAP71@GMAIL.COM
TELEGRAM @KALTUBE_BOT
CHANNEL :- @KALTUBE

GRAPHICS DESIGN
MHGRAPHICS
MHGRAPHICS1@GMAIL.COM
DIAL :- (+251) 920019699
TELEGRAM :- @MHGRAPHICS

" ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም
ተሞልቶ በእኛ አደረ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 1:14)



# ቤተክርስቲያን ማን ናት?

በኣበይ መሳይ አለማየሁ



ቤተክርስቲያን በክርሰቶስ ኢየሱስ አዳኝነትና ጌትነት አምነው የዘላለም ህይወት ለመውረስ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል ከዓለም ተጠርተው የወጡ ሰዎች ጉባኤ ናት።የአዲስኪዳን መጻሐፍት በተጻፉበት በግሪክ ቋንቋ ቤተክርስቲያንን “ኤክሌሺያ” የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ ትርጉሙም “ያመኑ ሰዎች ስብስብ” ማለት ነው። እናም ቤተክርስቲያን ተብሎ ሲነገር እየተነገረ ያለው ስላመኑ ሰዎች ስብስብ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር  የታወቀችና እውነተኛ አማኞችን የምታቅፍ የክርስቶስ አካል ስትሆን ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው (ኤፌ.1፡20-23፡ 5፡27፤ቆላ.1፡18፤ ማቴ.16፡18፤ 1ጢሞ.3፡15) ቤተክርስቲያን የተጠመቁ አማኞችን ያቀፈች ፣ የጥምቀትና የጌታራት ስርዓቶችን የምትፈጽም፣ ለክርስቶስ ትምህርት ራሷን በመስጠት የምታመልክ፣ወንጌልን በአለም ዙሪያ የምታደርስ፣ የራስዋ መሪዎች ያሏት፣አስተዳደር ያላት፣ ለአለም ሰላም የምትጸልይ፣ በችግር ላይ ያሉትን የምትረዳ የክርስቶስ አካል ናት (ፊል.1፡1፤ 1ተሰ.1፡1፤ 1ቆሮ. 1፡2፤ ቆላ.4፡15)።

## የቤተክርስቲያን የተለያዩ ስሞች

ቤተክርስቲያን የተገለጸችባቸው የተለያዩ ስሞች አሉ።ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ከሚኖራት ግኑኝነት አኳያ በተለያዩ ምሳሌዎች ተገልጻለች። እነዚህ ምሳሌዎች ዘርፈ ብዙ የሆነውን የቤተክርስቲያን ባህሪይን ያሳያሉ።እነሱም :-

1, የእግዚአብሔር ህዝብ ነች፡-

ቤተክርስቲያን በዚህ ምሳሌ መገለጿ በምእመናን ላይ የባለቤትነት መብት ያለዉ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ለማመላከት ሲሆን ማንም ሰው የቱንም ያህል ሰዎችን ወደ ጌታ በማምጣትና ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም የባለቤትነት መብት የሌለው መሆኑንም ይጠቁመናል። ምእመናንም የእግዚአብሔር እንደሆንን በማሰብ ለእርሱ መኖር አለብን። (2ቆሮ.6፡16)

2, ክርስቶስ ራስ የሆነበት አካል ነች

ይህ ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ የአካል ክፍሎች /ብልቶች/ የተገናኙች መሆኑ አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤ (1ኛቆሮ12:12)

እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው።ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1፡18 ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።(ኤፌ5 : 23)

3, የወይን ቅርንጫፍ ነች
ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን የወይን ግንድ አብን የወይን ተክል ባለቤትና ገበሬ፣ በእሱ የሚያምኑትን ደግሞ የወይን ተክል ቅርንጫፍ በማድረግ ያቀርባል ። ፍሬ የሚገኘው በቅርንጫፉ ላይ እንደሆነ በማስረዳት ቅርንጫፎች በወይን ግንዱ ላይ በመጣበቅ የሚፈለግባቸውን ፍሬ እንዲያፈሩ ይመክራል። ይህ የሚያመለክተው ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላትን ህይወት፣ ፍሬ የሚያፈራ ጠንካራ ህብረት መሆኑ ያሳያል። ( ዮሐ.15፡1-11)፡

## የአጥብያ ቤተክርስቲያን ተግባራት

ቤተክርስቲያን ከመሰረታትና ሙሉ ባለቤትነት ካለው ከክርስቶስ ተልዕኮ ወይም ተግባራት ተሰጥቷል። እነዚህ ተግባራት በስራ ላይ ሲውሉ እግዚአብሔር ይከብራል። የሰው ልጆችም የእግዚአብሔርን መልካምነት ተገንዝበው ክብርን ለእሱ ይሰጣሉ።

ቤተክርስቲያን የተሰጣትንም ተግባራት በአምስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።
የቤተ ክርስቲያን ተግባራት ማለት የእያንዳንዱ አማኝ በተናጠል እንደዚሁም በጋራ የሚከናወን ተግባር ነው። ( ማቴ.22፡33-40፤ 28፡19-20)።

1, እግዚአብሔርን ማምለክ
ሰዎች ከተጠሩበት አላማ አንዱ ወደውና ፈቅደው እግዚአብሄርን እንዲያመልኩ ነው ( ዘጸ 20፡3) ቤተክርስቲያንም ያሙኑ ሰዎች ስብስብ እንደመሆኗ ከተግባሮቸዋ አንዱ እግዚአብሄርን በመሰባሰብ ማምለክ ነው ( ማቴ.4፡10፤ ዮሐ.4፡22-24)። በአንድ ልብ በጋራ የሚደረገውን አምልኮ እግዚአብሄር በላቀ ሁኔታ እንደሚባርከው ቃል ገብቷል ( መዝ133፡1-3) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጋራ አምልኮ እያሽቆለቆ መጥቷል። ለዚህ ዋና ምክንያት በታዋቂ ሰባኪዎች በቴለቪዥን የሚተላለፉ ስብከቶች በይዘታቸው የተሻሉ እንደሆኑ ስለሚታሰብና በሌሎችም ምክንያት ነው።

2, ወንጌልን ማሰራጨት
ቤተክርስቲያን የምትሰፋበትና ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው ድነት የሚያገኙበት መንገዶች ብዙ ናቸው ወንጌልን ለሰዎች የሚሰበከው በቃል ፣ በጽሁፍ ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች እና በመልካም አኗኗራችን የወንጌል እውነት ሲቀርብላቸው ነው።። ( ሮሜ.10፡14-16፤ ማቴ.5፡13-16) በመሆኑም ወንጌልን ማሰራጨት ከቤተክርስቲያን ተግባራት አንዱ ሲሆን፣ ለማሰራጨት እንቅስቃሴ ሲደረግ አብዛኛውን ጊዜ ከማያምኑት ወገን ተቃውሞንም ያስነሳል። ይሁንና ሊመጣ የሚችለውን ተቃዉሞ በመቋቋም ወንጌል መስበክ አለባት ( ሐዋ.4፡1-20)። ወንጌልን ማሰራጨት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ ኃላፊነት ሳይሆን ምዕመናን በሙሉ የሚሳተፉበት ተግባር ነው ( ማቴ.28፡19-20፤ ማር.16፡15፤ ሉቃ.24፡47-49፤ ዮሐ.20፡21፤ ሐዋ.4፡8) ወንጌልን መስበክ መስዋዕትነትን ቢጠይቅም ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ በረከትንም ያስገኛል።

3, ደቀመዝሙር ማድረግ
ሰዎች ድነት ካገኙ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል በመማር በጌታ ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመንፈሳዊ ህይወታቸው ሊያድጉና ክርስቲያናዊ ባህሪ ሊያሳዩ እንደሚገባ ከጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ ተሰጥቷል ( ማቴ.29፡ 19-20) ይህ ሂደት ደቀመዝሙር ማድረግ ይባላል። ምዕመናን በራሳቸው ተነሳሽነት በግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ቤተክርስቲያን ደግሞ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት፣ በመምከርና ስህተት ሲሰሩ እርምት በመስጠት ምእመናንን በሙሉ ደቀመዝሙር ማድረግ አለባት። ቤተክርስቲያን ምእመናንን ደቀመዝሙር ማድረግ ከቻለች ፣የቤተክርስቲያን ተግባራት በነሱ የሚፈጸሙ ስለሚሆን ወደ ቀጣዩ ትውልድ የሚደረገው የወንጌል ቅብብሎሹ ውጤታማ ይሆናል።

4, ሌሎችን ማገልገልና በጎ ተግባራትን መስራት

ወንጌል የምሰራቹን ዜና ማብሰርና ያመኑትን ደቀመዝሙር ማድረግ ማለት ቢሆንም ወንጌላችን የተሟላ ነው ማለት የሚቻለው በተለያየ የኑሮ ችግር ውስጥ ያሉትን አቅም በፈቀደ መጠን ከገጠማቸው ችግር ወጥተው ለሌሎች የሚተርፉ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ መርዳት ነው። ጌታ ኢየሱስ "በፍርድ ቀን ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁንም" በማለት እውነተኛ ክርስቲና ለሰዎች ቸርነት ማድረግ መሆኑን በግልጽ ያሳያል ( ኤፌ.4፡12፤ ማቴ.10፡35-40፤ 25፡35-45፤ ሉቃ.10፡25-37፤ ያዕ.1፡27)።

በጎ ስራዎች ወይም በድህነት ውስጥ ያሉ ወገኖችን ማገዝን ስናስብ ብዙውን ጊዜ ወደ አእምሯችን የሚመጣው ከባህር ማዶ በሚገኝ ገንዘብና በተደራጀ የልማት መርሃ ግብር የተለያዩ ፕሮጄክቶችን ማካሄድ ነው። ይሁንና በግልና በቤተሰብ ደረጃ አቅም በፈቀደ መጠን በአቅራቢያችን የሚገኙ ድሆችን ከድህነት እንዲወጡ መርዳት ይጠበቅብናል።

5, ለአለም ሁሉ መፀለይ

ቤተክርስቲያን ለቅዱሳን ለሃገርና ለመንግስት ባለስልጣናት ትፀልያለች የሃገር ሰላም፤ ለመልካም አስተዳደር ፤ ስነምግባር እና መልካም አስተዳዳሪዎች ከእግዚአብሔር የሚሰጡ በመሆኑ ቤ/ክ አጥብቃ መፀለይ ስራዋ ነው። ( ሮሜ. 13፡1-7፤ኤፌ.6፡18-20)

## የቤተክርስቲያን እውነታዎችና ተግዳሮቶች

ቤተክርቲያን ከመሰረታትና ሙሉ ባለቤትነት ካለው ከክርስቶስ ተልዕኮ ተሰጥቷት በምድር ላይ ያለች የክርስቶስ አካል ነች፣ቤተክርስትያን ላለፉት 2000አመታት በብዙ ድልና በብዙ ውጣውረድ እንዲሁም በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፋለች አሁንም እያለፈች ነው።ቤተክርስቲያን የሰው አይደለችም፣የሐዋርያ፣የፓስተርም የነብይም፣ የወንጌላዊም የአስተማሪም አይደለችም፤ ነገር ግን ሰው ሊያስተዳድራት ይችላል፤ እንዲሁም መጽሐፍቅዱሳችን ቤተክርስቲያን ለሰራችው መልካምም ሆነ እንደ እግዚአብሔር ቃል ባልተመላለሰችበት ጉዳይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ብድራትን እንደምት ቀበል ያስተምራል፤ ቤተክርስቲያን  በአገልግሎቷ፣ በአካሄዷ፣ በሃላፊነቷ፣ በተሰጣት የጸጋ ስጦታ ና በተሰጣት መንፈሳዊ ስልጣንና ኃይል ጉዳይ በኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ትቆማለች፣ በዚህ የፍርድ ወንበር ፊት ትዳኛለች ትጠየቃለች ፣ከዛም እንደስራዋ ታገኛለች፤ያ ማለት ግን ቤተክርስቲያን የምትዳኘው በሽልማት ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው ይህ ማለት ቤተክርስቲያን በነጩ ዙፋን ፍርድ ፊት ቆማ አይደለም የምትዳኘ ው፣ ''ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና።ሮሜ 14 ፡10

እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።" ( ሮሜ 14 ፡ 12)

በራዕይ መጽሐፍ ላይ ሰባት አብያተክ ርስቲያናት ተጠቅሰዋል፣ የኤፌሶን ቤ/ክ፣ ሰምርኔስ ቤ/ክ፣ ጴርጋሞን ቤ/ክ ፣ትያጥሮን ቤ/ክ፣ ሰርዴስ ቤ/ክ፣ የፊልድልፍያ ቤ/ክ፡ሎዶቅያ ቤ/ክ ናቸው።

እነዚህ ሰባቱ አብያተክርስቲያናት በወቅቱ በትንሹ እስያ የሚገኙ አጥቢያዎች ነበሩ፤ እያንዳንዳቸው አብያተክርስቲያናት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ነበራቸው፣ኢየሱስም ለጠንካራ ጎናቸው ማበረታቻ ለደካማ ጎኖቻቸው ደግሞ ምክር ሲሰጥና ሲገስጽ እንመለከታለን።

1  የኤፌሶን ቤተክርስቲያን

የኤፌሶን ቤ/ክ ስንመለከት የኤፌሶን ቤ/ክ  ለክርስቶስ ስም ስትል ጸንታ የቆመች፣ ሐዋርያት ነን ባዮችን መርምራ አለመሆናቸውን የምታጋልጥ፣ ፤ያልደከመች ቤ/ክ ነበረች፤ግን የቀድሞ ፍቅሯን ትታለች፤ለዚህም ውድቀቷ ከወዴት እንደ ወደቀች እንድታስብ ንስሐም እንድትገባ የቀደመውን ሥራዋን እንድታደርግ፤ አለዚያ እንደሚመጣባት ንስሐም ባትገባ መቅረዝዋን ከስፍራው እንደሚወስድ ማስጠንቀቂያ ደርሷታል።ራእይ 2:1-5   የኤፌሶን ቤ/ክ በወቅቱ በትንሹ ኤስያ የምትገኝ ከተማ ነበረች፣ ኤፌሶን የንግድና ከሶስቱ የሮም ግዛቶች በጣም ዝነኛ ነበረች፣ኤፌሶን ከተማ የአርጤምስ ቤተ ጣኦት መገኛ ነበረች(ሐዋ19:21-41)

2, ሰምርኔስ ቤተክርስቲያን
የሰምርኔስ ከተማ ከኤፌሶን በስተምዕራብ በኩል በ25ማይል ርቀት ትገኝ ነበር፤በዚህ ከተማ ቤ/ክ ከሁለት ዋና ዋና ችግሮች ጋር ትጋፈጥ ነበር 1ኛ የአይሁድ ክርስትናን መቃወምና አይሁድ ያልሆኑ አምልኮተ ንጉስን መቀበላቸው ዋና ዋና ችግሮች ነበሩ፤( ራዕይ 2:9)

3 የፔርጋሞን ቤተክርስቲያን
የፔርጋሞን ከተማ በ1000ጫማ ከፍታ ባለው ከተማ ላይ የተመሰረተች ከተማ ነበረች፣ ከተማዋ የግሪክ ባህልና ስልጣኔ ማዕከል ነበረች፣ ከተማዋ የተለያዩ አይነት ጣኦቶች ነበሩባት፣ ፔርጋሞን በእባብ ራሱን በመሰለ ጣኦት የተሞላች ከተማ ነበረች፤ አማኞች በዚህ ከተማ ታላቅ ስደትና እምነታቸውን እንዲተው ግፊት ይደረግባቸው ነበር፣ በፔርጋሞን ይገኙ የነበሩ አማኞች በእምነታቸው ተመስክሮላቸዋ ል የተወቀሰችበትም ነገር አለ አንደኛውም በስህተት ትምህርትና በስነምግባር ጉድለት ነው።

4 የትያጥሮን ቤተክርስቲያን
ትያጥሮን በጥንት በሮማውያን የኤዥያ ግዛቶች ውስጥ አንዷ የነበረች ባለጠጋ ከተማ ነበረች። ይህች ከተማ በአሁኑ ወቅት ቱርክ ነች።
ለዚህች ቤ/ክ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠንካራ እና ደካማ ጎኗን በማንሳት ከደከመችበት ሁኔታ እንድትወጣ አምላካዊ ምክር ሲመክርና ሲገስጽ እናነባለን። ( ራዕይ 2:20-22)
የትያጥሮን ቤተክርስቲያን 5 ዋና ዋና ጠንካራ ጎኖች
1 ፍቅር 2 እምነት 3 አገልግሎት 4 ትዕግሥት 5 ታላቅ ስራ
በመቀጠል ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህችን ቤ/ክ ሃጢአት/ውድቀት ይጠቅሳል።
''ዳሩ ግን ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተም ረውንና የምታስተውን ያችን ሴት
ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ''
በወቅቱ ሐሰተኛ ነብያቶች፣ጣኦት የሚያመልኩ፣ግልሙትና ውስጥ የገቡ ክርስቲያኖች በቤተክርስትያን ውስጥ ነበሩ።

5,የሰርዴስ ቤተክርስቲያን
የሰርዴስ ከተማ በወቅቱ ባለጠጋ የንግድ ከተማ እና በሙስና የምትታወቅ ከተማ ነበረች።የሰርዴስ ቤ/ክ ዋና ችግር
'' ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ሊሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና።''' (ራእይ 3:1,2)

6, የፊልድልፊያ ቤተክርስቲያን
,የፊልድልፊያ ከተማ በፔርጋሞን ህዝቦች የተመሰረተች ከተማ ነበረች ከተማዋ ከዘመናት በኋላ በመሬት መንቀጥቀጥ ልትጠፋ ችላለች፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህች ቤ/ክ ማበረታቻ እና ዋና ዋና ምክሮችን ይመክራታል።( ራዕይ 3:8-9)

7,የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን
የሎዶቅያ ከተማ በባንክ ሴልጣኔና በጥጥ ንግድ እንዲሁም በህክምና ት/ት በተለይ በአይን ኩል ገናና ነበረች፣ የቤ/ክ ዋና ችግር የአቋም ችግር ነበር። ወይ ቀዝቃዛ አልሆነች ወይ ሙቅ/ትኩስ/ አልሆነች።ሌላው የዚህች ቤ/ክ ድክመት ሃብታም ነኝ አንዳች አያስፈልገኝም ባይ መሆኗ ነው፣ ቤ/ክ ይህን ትበል እንጂ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላታል። ( ራዕይ 3:16)
''' ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥'' ( ራእይ 3 : 17)

ከላይ በራዕይ መጽሐፍ ላይ የተመለከትናቸው ሰባቱ አብያተክርስቲያናት ምን እንማርባቸዋለን?

1, ፍቅር ላይ ያልተመሰረተ አገልግሎት፣እምነት፣ዕናት፣ትጋት ከንቱ እንደሆነ እንማራለን።
2, ቤተክርስቲያን ለሰራችው ድልም ሽንፈት ከኢየሱስ የምትቀበለው ብድራት እንዳለ መማር እንችላለን።
3, ቤተክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣት አላማ ላይ የሙጥኝ ብላ አላማዋን ከግብ ማድረስ እንዳለባት
4, ቤ/ክ የእምነት ተጋድሎን በሚገባ መታገል እንዳለባት መማር እንችላለን
5,ቤተክርስቲያን በአስተምህሮ፣በአካሄዷ፣አቋም ያላት የጸናች መሆን እንዳለባት መማር እንችላለን።
6, ቤተክርስቲያን የትኛውንም አይነት የዲያብሎስ አሰራር መቃወምና መተባበር እንደሌለባት
7, ቤ/ክ ከመንግሥት፣ከቤተሰብ፣
ከግለሰብ የተለያዩ አይነት ተቃውሞ ሊደርስባት ይችላል ቢሆንም ግን ጌታ እንደተናገረን መፍራት እና ወደ ኋላ ማፈግፈግ እንደሌለብን እንማራለን።
8, ቤ/ክ የሃሰት ትምህርቶችን በመቃወም ጤናማው ት/ት መከተል እንዳለባት ያስተምረናል።
9, የተለያዩ አጋንንታዊ ልምምዶች ቤተክርስቲያን ልትቃወም ይገባል ለምሳሌ በጴርጋሞን ቤ/ክ በወቅቱ ፈውስ ለመቀበል በተሳሳተ ት/ት ራሱን አዳኝ ነኝ ብሎ ወደሚጠራው እባብ ይሄዱ ነበር።



STAYHOME
SAVELIVES

አለማችንን እያሳሰበ ያለው የኮሮና ቫይረስ የለም ከሚሉ የተሳሳቱ መንፈሳዊ ካባ የተላበሱ መረጃዎች ራስዎንና ቤተሰብዎን ይጠብቁ ።



# ማህበራዊ ሚዲያና ክርስትና

በ ዘሪሁን ግርማ

ይህ ርዕስ ሰፋ ያለና ሐሳብና ትልቅ ስራ እንደሚፈልግ የታወቀ ነው። ማህበራዊ ድህረ ገጽ የአለማችን ትልቁ ስጋትም ጭምር እየሆነ ነው። አብሶ ለነገ ትውልዶች። ዘመኑ የማህበራዊ ትስስር ዘመን ነው። ለዛም ደግሞ በጣም ብዙ ማህበራዊ ድህረ ገጾች አሉ። ፌስ ብክ (Facebook) ቴሌግራም (Telegram) ፤ ዩቲዩብ (YouTube) ቲክቶክ (Tik Tok) ኢንስታግራም (Instagram) ወዘተ እያልን መቀጠል እንችላለን። የእነዚህ ነገሮች መፈጠር ራሱን የቻለ ጥቅም ያለው መሆኑ እሙን ነው። አብሮ ግን ተያይዞ የትውልድን አቅጣጫ የሚያስቀይሩና የሚበላሹ ነነሮች እያየን ነው። በመጀመሪያ እንደ ክርስቲያን ማህበራዊ ድህረ ገጽን እንዴት ለትውልድ በሚጠቅም መልኩ፤ እንዴት የክርስትና ህይወትንና ስነምግባርን በማይነካ መልኩ፤ ይልቅ ለክርስትናችን በሚጠቅም መልኩ ልንጠቀመው እንችላለን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብን።

በአለም ደረጃ ያሉ ከክርስትና ውጪ ያሉ ሐይማኖቶች ሐሳባቸውንና እምነታቸውን፣ ሌሎቹ አለማዊነትንና (የወንድ ለወንድና የሴት ሴት ጋብቻን) ለማስፋፋት ወይም የርኩሰትን ሐሳብ በትውልድ መሐል ለማስረጽ ማህበራዊ ድህረ ገጽን ግብ አድርገው እቅድ ይዘው ይሰራሉ። በአሁን ሰአት ብዙው ወጣት ያለው ማህበራዊ ድህረገ ገጽ ላይ ነውና። እንግዲህ የሶሻል ሚዲያ አደጋው ከፍ እያለ መቷል። እንደ ክርስቲያን ማህበራዊ ድህረ ገጽ መጠቀም መልካም ቢሆንም እጅግ ታላቅ ጥንቃቄና ሐላፊነት አብሮ ግን አለው። ማህበራዊ ድህረ ገጽን አለም ለምትፈልገው አላማ እየተጠቀመችበት እንዳሉ የታወቀ ነው። ክርስቲያኖችስ ቤተክርስቲያንስ ይህን ነገር እንዴት መጠቀም አለባት? የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነው። ማህበራዊ ድህረ ገጽ ልክ እንደ እሳት አድርገን ልንወስደው እንችላለን ከአግባቡ ከተጠቀምንበት ለብዙ ነገር ይጠቅማል ያለ አግባብ ከተጠቀምንበት ሊያጠፋን ሁሉ ይችላል።

## የማህበራዊ ድህረ ገጽ ሱስ

ማህበራዊ ድህረ ገጽ ከመገልገያነት ወደ ሱስ ካደገ ሁለንተናችንን ተቆጣጥሮናል ማለት ነው።
ልክ እንደ ኮኬይን፤ ወይም እንደ ጫት ወዘተ ማለት ነው። ማህበራዊ ድህረ ገጽን እየተቆጣርነው ካልተጠቀምንበት ጊዜያችንን፤ ገንዘባችንን፣ ለጸሎት መጽሐፍት ለማንበብ የሚኖረንን ጊዜ፤ ለማህበራዊ ግንኙነት የሚንረንን ጊዜ፤ ህይወት የሰጠችንን ጤናማና ተፈጥሮአዊ ግንኙነት እንዳንጠቀም ጭንቅላታችንን መረጃ መረብ (Internet) ውስጥ እንድቀብር ያደርገናል። ይህ ሱስ ብዙዎችን ብቸኛ እንዲሆና፤ በራስ መተማመን እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ ለብዙ ትዳር መፍረስ፤ (አንደኛው ምክንያት ከሚስት ውጪ ሌላ ግንኙነት በማህበራዊ ድህረ ገጽ አማካኝነት መፍጠር ሲሆን ሌላው pornography ነው።) ብዙ ወጣቶችም ላለማግባታቸው ምክንያት ሆኗል።

ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባ ጤናማ የህብረት ግንኙነት በማህበራዊ ድህረ ገጽ ምክንያት እየጠፋ ሰዎች የውሸት ግንኙነት እየበረከተ እየመጣ ነው። ሰው በባህሪው ከሰዎች ጋር በአካል ተገናኝቶ እንዲኖር የተፈጠረ ሲሆን ይህ ነገር በርዞታል ማለት እንችላለን። ማህበራዊ ሚዲያዎችን ሰዎችን ለመጥቀምና ወንጌልን ለማስተማር መጠቀም እንደ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው። ከዛ ውጪ ባሪያዎች ነን።

## ለውሸት መረጃ መጋለጥ

ማህበራዊ ድህረ ገጽ አንደኛውና አስቸጋሪ ነገሩ ለተሳሳተና ለውሸት መረጃ ማጋለጡ ነው። በዚህ ጊዜ ብዙው ሰው ሁሉ ስልክ፣ ላፕቶፕና ኢንተርኔት ያገኛል። ከዚህ የተነሳ ሁሉም ሰው የመሰለውም የፈለገውን መረጃ ይለቃል። ትውልድ የማመዛዘን
አቅሙ ካላደገ ተወደደም ተጠላም ለሚለቀቁ የስህተት መረጃዎች ይጋለጣል። መረጃ ደግሞ ሐሳብን ሐሳብ ደግሞ ማንነትን ይገነባል። ስለዚህ እንደ ክርስቲያን ያየነውን ሁሉ ማንበብና ማየት አላስፈላጊ ነው። ዩቲበሮቻችን የሰዎችን ተመልካችነት (Attention) ለማግኘት ያለ የሌለ ርዕስ ይሰጣሉ። ብዙ ክርስቲያን ጸሐፍትና ቪዲዮ የሚሰሩ አካላት ለአካሉ ከሚጠቅም ነገር ይልቅ የመሰላቸውን ሲጽፉና ሲናገሩ ይታያሉ። ስለዚህ ክርስቲያን ምን እንዲዲያን ምን እንዲሰማ ሊጠነቀቅ ይገባዋል። ስለዚህም አህምሮአችንን ለክፉ ሐሳብ ባሪያ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባናል።

## ሰው ከሶሻል ሚዳያ ሱስ ራሱን ማዳን ይችላል?

ማንኛውም ሱስ የመጀመሪያ ልንተወው ስንል ብዙ አይነት ስሜት ሊሰማን ይችላል። መጨነቅ መደበት መደበር ባዶነት ወዘተ። ግን ያም ስሜት የሚሰማን ለጥቂት ጊዜ ነው። ክርስቲያን ማህበራዊ ሚዲያዎችን በተገቢውና ህይወቱን ባልተቆጣጠረ መልኩ ሊጠቀምበት ይችላል። ብዙዎቻችን ስልኮቻችን ላይ ማንኛውም ማህበራዊ ድህረ ገጽ ሳንከፍት የመቆየት ልምድ ማዳበር አለብን።
ክርስቲያን ማህበራዊ ሚዲያን በሚፈልገው ጊዜና አግባብ ባለው ሁኔታ ሊጠቀምበት ይገባል። ከማህበራዊ ድህረ ገጽ ሱስ ለመራቅ ይጠቅማሉ የምላቸውም ጥቂት ጥበቦች ላካፍላችሁ።

፨አህምሮአችሁ በሌላ ስራ እንዲጠመድ ማድረግ
፨ማንበብና መጸለይ፤ መንፈሳዊ ነገሮችን ማሰላለሰል አብሶ ማታ ላይ ጸልየንና ቃል አንብበን ለመተኛት አህምሮአችንን በማህበራዊ ገጽ ወሬ ማንጻት ይኖርብናል።
፨በየዕለቱ ልናከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች ላይ ማተኮር
፨ ማህበራዊ ሚዲያዎችን ስንጠቀም አስፈላጊና ማየት ወይም ማስተላላፍ የሚገቡ ነገሮችን አስላልፈን መውጣት።
፨ አህምሮአችንን የማህበራዊ ድህረ ገጽ ጥገኛ አለማድረግ
፨ ከሰዎች ጋር ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አብሮ ማሳለፍ ማውራት ሐሳቦችም መከፋፈል ወዘተ

ሱስ ሁልጊዜ ለተገዛንለት ነገር ባሪያ መሆን ነውና በብዙ ራሳችንን መጠበቅ አለብን።

*********



# እግዚአብሔር
## በህይወታችን ያለውን ፈቃድ
## እንዴት እናውቃለን?

በአቤኔዘር አለማየሁ

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናውቅበት የምንችልባቸው አምስት ቀላል መንገዶች እናያለን
(መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 3)
5፤ እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም፤ እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ።
6፤ ከሚከብቡኝ ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም።

እንዴት እግዚአብሔር በህይወቴ ስላለው ፈቃድ ስለማወቄ እርግጠኛ መሆን እችላለሁ? ማለትም በመጨረሻም የኔ ፈቃድ ቢሆንስ ፤እኔን ለማደናቀፍ ጠላት ለመናገር እየሞከረ ሊሆን ይችላል እና ስለዚህም በህይወታችን የአምላክን ፈቃድ ማስተዋል የምንችልባቸው አምስት ቀላል መንገዶችን ላካፍላችሁ ወደድኩ።

### #1 እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ይናገራል

የመጀመሪያውን ስናይ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ይናገረናል ይህም ማለት የእርሱ ፈቃድ ከቃሉ ጋር ፈፅሞ ስለማይቃረን።እስኪ ለምሳሌ በትዳር ውስጥ ናቹ እንበልና በማንኛችሁም በኩል ምንዝርና የለም ፤ ከዛም አንደኛቹ "እኔ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ አልተሰማኝም እናም ከዚህ በላይ በትዳር መቆየት አንችልም" ብትሉ ጉዳዩ ይሄ እንዳልሆነ እናውቃለን ምክንያቱም እርሱ በቃሉ እንደሚለው እግዚአብሔር ፍቺን ይጠላል ፤ ስለዚህ ነው ቃሉን ማንበብ ለኛ ወሳኝ የሚሆነው ፤ ቃሉን በጣም ማጥናት ፣ ወደፊትም ወደኋላም ማወቅ ያስፈልጋል። ቃሉን በይበልጥ ባወቅን ቁጥር የበለጠ በህይወታችን ስላለው ፈቃድ ማስተዋል እንችላለን። የሚያስደንቀው ደግሞ አብዛኛው አምላካዊ ህይወትና እንድንኖር ማወቅ የምንፈልገውን እግዚአብሔር በቃሉ አስቀድሞ ገልጦልናል። ስለ ወሲባዊ ንፅህና ፈቃዱ ምን እንደሆነ ይነግረናል (1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ምዕራፍ 4:3-8) ፤ ደቀመዛሙርት ማፍራት አለብን ይህም የእርሱ ፈቃድ ነው (የማቴዎስ ወንጌል 28:18-20) ፤ ማገልገል ፣ እምነታችንን ማካፈል (2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4:5) ስለ ባል እና ሚስት መዋደድ (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5:32) ፤ በመደበኛነት ለአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን መስጠት (2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9:1-6) ፤ በመንፈሳዊ ስጦታዎችን በመጠቀም ማገልገል (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 12-14)። ብዙ ጊዜ እንዲህ በማለታችን ጥፋተኞች ነን " እግዚአብሔር ሆይ አንተ የበለጠ እንዲሁም በጣም የበለጠ እንድትገልጥልኝ እፈልጋለሁ" እግዚአብሔርም ሲናገር "ስማኝ ቀድሞውንም ተገልጦልህ የነበረውን እንኳ አየታዘዝክ አይደለም" ይህም ራሳችንን እንድንጠይቅ ያደርገናል "ለምን እግዚአብሔር ከዚህ የበለጠ ይግለጥልን?"

## # 2 እግዚአብሔር በፆም ይናገራል

በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ የሚናገረን ከእርሱ ጋር በቅርብ ግንኙነት እንዲሁም በፆም ነው (መጽሐፈ ምሳሌ 3:3)።እንበልና ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ያሳለፋችሁት ጊዜ የለም ከዚያም ትልቅ ውሳኔ መወሰን አለባችሁ ከዛም ተስፋ በመቁረጥ ወደ እግዚአብሔር ሄዳችሁ ከእርሱ የሆነ መልስ አገኛ ይሆን በሚል ተስፋ ፤ ብዙውን ጊዜ በዚያ መንገድ አይሰራም። እግዚአብሔርን ጥልቀ ደረጃ ከፈለግን (የማቴዎስ ወንጌል 7:7) እና በጣም በትጋት ስንፆም ወይም መደበኛ ፣ ወጥነት ኖሮን ከእግዚአብሔር በቅርበት ባሳለፍናቸው በነዚያ ወቅቶች የእርሱን ፈቃድ ይገልጥልናል እናም በግልፅ ይናገረናል። ስለዚህም መርሁ ይህ ነው: በመደበኛነት ጊዜያቸውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያሳልፉ ሰዎች በመደበኛነት ለፀሎታቸው ምላሽን ያገኛሉ።

## # 3 እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ይናገራል

እግዚአብሔር ለእኛ ከሚናገርበት ሦስተኛው መንገድ በመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ድምፅ ነው (ወደ ገላትያ ሰዎች 5:16) ፤ ይህ በጣም መንፈሳዊ እንደሆነ እንደምታስቡ ይገባኛል ግን ከእርሱ ጋር ይበልጥ ስንገናኝ ይበልጡኑ ራሱን ይገልጥልናል። የእርሱንም ፈቃድ ይገልጥልናል (ወደ ገላትያ ሰዎች 5:25)። ማንን ማናገር እንዳለብን ፣ እንዴት ነገሮችን መናገር እንደሚያስፈልግ ፣ መቼ ነገሮችን መናገር እንዳለብን ፣ ማንን ማመን እንዲሁም አለማመን እንዳለብን ፣ መሄድ ስላሉብን ቦታዎች ፣ ማድረግ ስላለብንና ስለሌሉብን ነገሮች ፤በምንፈተንበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን እንዲሁም እንዴት ፈተናዎችን ማስወገድ እንዳለብን እና ሌሎችም። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን በቆየን ቁጥር እርሱም ሁልጊዜ ይናገረናል እንዲሁም ምን መወሰን እንዳለብን በመደበኛነት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ይገልጥልናል።

## # 4 እግዚአብሔር በሰዎች በኩል ይናገራል

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ከሚናገርበት መንገድ አራተኛው በሰዎች በኩል ነው። መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለን የመካሮች ብዛት ደህንነት ነው ይላል (መጽሐፈ ምሳሌ 11:14) ። አንዳንድ በህይወቴ በጣም አስፈላጊ ውሳኔዎችን የምወስነው ታማኝ የሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎችን ካማከርኩ በኋላ ነው። አሁን እዚህ ላይ ቁልፉ ነገር የግድ የእግዚአብሔር ሰዎች መሆን አለባቸው የሚለው ነው። እነዚህም በባህሪያቸው እምነት የሚጣልባቸው መሆን ይኖርባቸዋል እንዲሁም ማንን ማመን እንዳለብን እግዚአብሔር ይናገረናል። እነሱ ግን ለኛ ውሳኔውን አይወስኑም። ስለዚህ ልታምኗቸው ምትችሏቸውን አምስት ሰዎች እንድትመርጡ ማበረታታት እፈልጋለሁ። በማንኛውም ጊዜ ጉዳይ ሲኖር ፣ችግር ካለ ወይም ትልቅ ውሳኔ ሲኖራችሁ ወደነሱ ወደምታምኗቸው ሄዳችሁ በውሳኔያችሁን ላይ የእግዚአብሔርን አመለካከት ሊያጋሩዋችሁ ይችላሉ።

## # 5 እግዚአብሔር በሁኔታዎች ውስጥ ይናገራል

አምስተኛውና የመጨረሻው መንገድ እግዚአብሔር የሚናገረው እና ፈቃዱን የሚገልጥልን በሁኔታዎች ውስጥ ነው። እግዚአብሔር በህይወታችን በሮች መክፈት ሲጀምር በተመሳሳይ ጊዜ ሌሎች የተወሰኑ በሮችን ይዘጋል (የዮሐንስ ራእይ 3:7)። እግዚአብሔር ብዙጊዜ የሚናገረን መንገድ "እንዲህ ነው እኔ የህይወታችሁ አቅጣጫ እንዲወርድ የምፈልገው ምክንያቱም እኔ ከሁኔታዎች ጀርባ ነገሮችን በማቀድ ስላለሁ እንዲሁም በእናንተ ፈንታ በዝርዝር ስለምሰራ።"ችግሩ አንዳንድ ጊዜ እኛ የፈለግነው በሮች እንወስናለን መንገዳችንንም ወደዛ ለማስገደድ እንሞክራለን ግን እነዚያን በሮች እግዚአብሔር አስቀድሞ ዘግቷቸዋል።

## እግዚአብሔር በህይወታችን ያለውን ፈቃድ ማወቅ እንችላለን?

ግን እንዴት እግዚአብሔር በኛ ህይወት ስላለው ፈቃድ እናውቃለን? ደህና ፤ እውነቱን ለመናገር አንዳንድ ጊዜ ሳስበው ይህን ነገር የተወሳሰበ ልናደርገው እንችላለን። እኔ  አንድ ማሳሰብ የምፈልገው ነገር በቀላሉ እግዚአብሔር በተለያየ ነገር እንዲያረጋግጥልን መጠየቅ ግን ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት እኛን ማግኘት እንደሚችል ስለሚያውቅ በእርሱ መተማመን አለብን ፤ ስለዚህ እርሱ ለኛ ሚያስተላልፈው መልዕክት ካለ ያስተላልፍልናል። ግን እስከዚያው ድረስ ባላችሁ ጥበብ እንዲሁም ባላችሁ እውቀት መጠን ምርጥ ውሳኔ እንድትወስኑ አበረታታችኋለሁ ፤ ምናልባት ውሳኔያችሁ ስህተት ቢሆን እግዚአብሔር አቅጣጫችሁን ይለውጠዋል እንዲሁም ትክክለኛውን መንገድ ይሰጣችኋል።

ምንጭ:- Allen Parr






# አስራስምንት

ሰላም አንባብያን! ይህ በቃልኛ መፅሔት በቤተክርስቲያንና በቅዱሳን መሀል በተለያየ አገልግሎት ዘርፍ ያሉ ሰዎችን እንግዳ አድርገን ከነሱ የህይወት ተሞክሮ የምንማርበት አምድ ነው። አስራስምንት ከሶስት አመት በፊት በወርሃ መስከረም የቃልቲዩብ ስርጭት የተጀመረበት የመጀመርያ ቀን በመወከል የዚህን አምድ ስም ሰይመናል። የዛሬዋ እንግዳችን ለተከታታይ አመታት ድንቅ ነጠላ ዝማሬዎችን ያደረሰችን ዘማሪት ስትሆን በቅርቡ "አባትነትህ" የተሰኘ አልበም በነፃ በዌዲሴ መተግበሪያ አድርሳለች። ዘማሪት ህይወት መለሰ በአገልግሎቷ እና በግል ህይወቷ እንዲሁም በሌሎች ሀሳቦች ከ ቃልኛ መፅሔት ጋር ቆይታ አድርጋለች። መልካም ንባብ!

ቃልኛ:-- ዘማሪት ህይወት በመጀመርያ ከውድ ጊዜሽ መስዋዕት አድርገሽ እንግዳችን ለመሆን ለቃለመጠይቃችን ፈቃደኛ ስለሆንሽ እንዲሁም ለዚ ቃለመጠይቅ ዝግጅት ስላደረግሽው ሁሉ በተከታታዮቻችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

ህይወት:- እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ቃልኛ :- ቀደም ወዳለው የህይወትሽ ክፍል ልውሰድሽና ተወልደሽ የነበረበትን አካባቢ የልጅነት የህይወትሽ እና አስተዳደግሽ ምን ይመስል እንደነበር አጫውችን

ህይወት:- እድገቴ በ Sunday School ነው። ይህም አሁን ላለው ህይወቴ መልካም ተፅእኖ አለው በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበር።

ቃልኛ :- ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝሽ አምነሽ የተቀበልሽበት ጊዜ መች ነበር? በህይወትሽ ላይ ምን ለውጥ አየሽ

ህይወት:- ጌታን ያገኘሁት ከቤተሰብ ማለትም ከመወለድ ነው። ጠንከር ያሉ አማኞች በመሆናቸው በጌታ ቤት ላለኝ እድገት ጠቅሞኛል።ህይወቴንም ከጌታ ቤት ውጪ አላውቀውም ከቀን ወደ ቀንም የህይወት ለውጥን አይቻለሁ

ቃልኛ :- ወደ ዝማሬ አገልግሎት እንዴት ገባሽ?

ህይወት:- ቀድሞ እንዳልኩህ ከ Sunday School ጀምሮና ሌላም ኳየር አገለግል ነበር። ነገር ግን የዝማሬ ህይወቴ Turning Point የሆነው የፓስተር ቤን ሂን "Good morning HolySpirit" መፅሐፍን ካነበብኩ ጀምሮ ነው። ለአንድ ክርስቲያን ለመኖርም ለአገልግሎትም በስራም በቢዝነስም ውጤታማ ለመሆን ቁልፉ ጌታ መንፈስቅዱስን ማወቅ ነው። መንፈስቅዱስ ከውስጥህ ዝማሬን ያፈልቃል። ሌላ ከውስጥህ የ Business ideaም ቢሆን ያፈልቃል። መንፈስቅዱስ በእያንዳንዱ ህይወታችን ውጤታማ እንድንሆን ነገሮችን ያደላድላል ያቀናጃል። የኔ የዝማሬ ህይወት በመንፈስቅዱስ መነካት ውጤት ብቻ ነው።

ቃልኛ :- አሁን የት ቤተክርስቲያን ነው የምታገለግይው? ከአገልግሎት ሌላ የምትሰሪው ስራ አለ ወይስ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነሽ?

ህይወት :- አሁን ሙሉ ትኩረቴ ወንጌል በገጠር ላይ ነው።

ቃልኛ :- ለአገልግሎቴ ምሳሌ ሆነውኛል የምትያቸው ሰዎች ወይም አገልጋዮች አሉ? እነማን ነበሩ?

ህይወት :- ዋናው የአገልግሎቴ ምሳሌ ክርስቶስ ነው። አገልግሎትን ሳስብ ሁልጊዜ የሚያነቃቃኝ መጽሐፍቅዱስ ነው። Joseph Prince , Benny Hinn እና Pastor Chris Andrewmac በጣም የማከብራቸውና ብዙ የተጠቀምኩባቸው የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። በዝማሬ አገልግሎታቸውና በስነምግባራቸውም ጭምር ዘማሪ ተስፋዬ ጋቢሶ እና ዘማሪት ሊሊ ጥላሁን የምባረክባቸው ናቸው።

ቃልኛ :- ስለ መጀመርያ አልበምሽ ስናነሳ... "አባትነትህ" በሰሞኑ ለቅዱሳን ያደረስሽው። እንዴት ነበር የተሰራበት ሂደት? ማን አገዘሽ?

ህይወት:- ባይገርምህ "አባትነትህ" አልበሙን በመስራት ሂደት ውስጥ የእውነት የእግዚአብሔር አባትነትን ያየሁበት ጊዜ ነበር። ባለቤቴ ኢሳያስ እኔን ሆኖ ማለት ይቻላል ማድረግ ያለብኝን ነገር በሙሉ ያደረገው እሱ ነው። ሙዚቀኛ ሱራፌል የሺጥላን ያገናኘኝ ጌታ ነው። እና እሱ የአልበሙን ስራ እጅግ በጣም ቀላል አደረገው እራሱ መጽሐፍቅዱስ ዝማሬዎቹን ከውስጡ አፈለቀ። እርሱ እኔ ሳልለፋና ሳልደክም ያለምንም እንግልት የአልበሙን ስራ አጠናቀቀው። ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን

ቃልኛ :-- ከዚሁ ጋር አያይዤ ሃዋ የዘመኑ ዘማሪያን ምንን እንዲመለከቱ በአገልግሎቱ አንቺ ከተማርሽው ምን ታስተላልፊያለሽ

ህይወት:- ዝማሬ ወይንም አምልኮ ከግጥምና ዜማ ከመፃፍ ያለፈ ነው። ከመጽሐፍቅዱስ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ይፈልጋል። እናም ህይወታችንን እና የተነካንበትን መዘመር እንዳለብን አስባለሁ። ለመዘመር መዘመር የለብንም። ግን መልዕክት ከጌታ ተቀብለን ለትውልድ ማስተላለፍ አለብን። አገልግሎት ከኛ አይደለም ተቀብለን የምንሰጠው ስለሆነ ለመቀበል ውድ የሆነ ጊዜ ከጌታ ጋር ሊኖረን ይገባል እላለሁ። ትህትና ትውልድን የምናከብር ራሳችንንም ዝቅ የምናደርግ መሆን አለብን። ጌታ ይሄንን እድል አምኖ ሲሰጠን ታማኝ መሆን አለብን። በፍቅርና በደስታ ማገልገል አለብን እላለሁ።

ቃልኛ :- ሃዋ ባለትዳርና የልጅ እናት ነሽ። በትዳር ውስጥ ተማርኩ የምትይው ትልቁ ነገር ምንድነው?



ህይወት :- እግዚአብሔርን ስለ ትዳሬ አመሰግነዋለሁ። ትዳር እግዚአብሔር የቋቋመውና የእግዚአብሔር ስጦታ እንደመሆኑ የክርስቲያን ትዳር ዋና አላማ የእግዚአብሔርን መንግስት አብሮ መስራት ነው። እኔም በዚ ጌታን እንዳገለግልበት መሆኑ በደንብ ገብቶኛል። ቤቴን የሚሰራው እርሱ ነው ይህ ቤት ደግሞ ከእግዚአብሔር ስለሆነ እርሱ የሚታይበት እና የሚከብርበት ነው። ትዳር ወንጌልን የመስበክ ሀይል አለው። እኔም ይሄን በደንብ ተረድቻለሁ እያቻለሁ

ቃልኛ :- እስኪ ስለ ወጣትነት እና መንፈሳዊነት እናንሳ ፤ እንዴት አብረው መሔድ ይችላሉ? በተለይም የወጣትነት እድሜ ለብዙ ስጋዊ ልምምዶች ለመሳብ ቅርብ ከመሆኑ አኳያ እንዴት ታይዋለሽ ሁለቱን

ህይወት:- ወጣትነት ማለት እግዚአብሔርም አለምም የሚፈልጉት ነው። ወጣትነት የብስለትና የሀይል ጊዜያችን ስለሆነ የነገ አካሄዳችንን ወይም ስኬታችንን የምንመርጥበት ቦታ ነው። ስለዚህ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። የውሳኔ ሰው መሆን አለብን። ወጣትነትን በስሜት ከተነዳን ከባድ እንደሚሆን ሁሉ በመንፈስቅዱስ ከተመራን በጣም አስደሳች ነው። ይህን ቅዱስና እውነተኛ ጥሪ መቀበል አለብን ይህ ከሆነ የእግዚአብሔርን የልብ ሀሳብ እናገኛለን።

ቃልኛ :- ብዙ ክርስቲያን ወጣቶች በቀላሉ በብዙ ነገር ሲረበሹ እና በቀላሉ ተስፋ ሲቆርጡ ይታያል እና ለዚህ ምክንያቱ ምን ይመስልሻል? እናም ስለ ተስፋ ምን ታስቢያለሽ? ተስፋ ቆርጠሽ ታውቂያለሽ?

ህይወት:- ተስፋችን ክርስቶስ ነው እርሱ ደግሞ ታማኝ ነው። ታማኝነቱንም ሁሉን መስቀል ላይ ፈፅሞ አሳይቷል። ተፈፀመም ብሏል። ያኔ አልቆልናል።ሁሉ ተከፍሏል። ስለዚህ ለነገ ብለን የምንጠብቀው ነገር የለም። የሚቀረው ነገር ቢኖር የኛ ማመንና መቀበል ነው። በእምነትና በትዕግስት የተሰራውን ነገር አውቀን መቀበል ነው። ስለዚህ ዳግመኛ የተወለደ ሁሉ ተስፋ የመቁረጥ ህይወት ውስጥ መግባት የለበትም። እኔ ተስፋ ቆርጬ አላውቅም። ይህን ያደረገው ጌታ ይመስገን። ለወጣቱ መልዕክቴ አይኖቻችንን ወደ ክርስቶስ መስቀል ማድረግ እንዳለብን አምናለሁ። ነገሮች ሁሉ እንዲሁ በነፃ ስለተከናወኑ ከራስ ከንቱ ትግል ወጥተው ወደ ፀጋው ዘፋን እንዲጠጉ እላለሁ። ያኔ ህይወት ቀላል ይሆናል። 2ቆሮ 4÷16

ቃልኛ :- በህይወትሽ ትልቅ ትምህርት ሆነውኝ አልፈዋል የምትያቸው ያሳለፍሻቸው ሁኔታና ገጠመኞች ካሉሽ አካፍይን ?

ህይወት:- በህይወቴ የተማርኩት ጊዜን ስለመጠቀም ነው። ጊዜን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። በከንቱ ያለፋትንና ያልተጠቀምኩባቸውን ጊዜያት መድገም አልፈልግም። እዚህ ምድር ላይ ለአላማ እንዳለሁ ከገባኝ ጊዜ ጀምሮ ጊዜውን በአግባቡና በስርአቱ መጠቀም ጀምሬያለሁ።

ቃልኛ :-- ሂዋ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምሽ ምን ይመስላል ለወንጌል ስራ አሁን እና ወደፊት በዚሁ ዘርፍ ላይ ምን ታስቢያለሽ? በተለይ አሁን ብዙሀኑ ሰው ጋር በቀላሉ ለመድረስ ቀላሉ መንገድ ማህበራዊ ሚድያዎች ከመሆናቸው አንፃር የቤተክርስቲያን ሚና የአገልጋዮችና ዘማሪዎች ድርሻ ምን መሆን አለበት

ህይወት :- ለወንጌል ሁሉንም መንገድ መጠቀም እንዳለብኝ አምናለሁ። ስለዚህም ማህበራዊ ሚዲያዎችን ሙሉ ለሙሉ በደንብ ለወንጌል እጠቀማለሁ። FaceBook Instagram Telegram እና ሌሎችንም ማህበራዊ ሚዲያዎችን አክብሬ ለወንጌል ስራ አውላቸዋለሁ። በዚህ አገልግሎቴም ብዙ የህይወት ምስክርነቶችንም ሰምቻለሁ። ስለዚህ ሁላችንም ክርስቲያኖች እና አገልጋዮች ይሄንን እድል ከቀልድና ፌዝ አልፈን ለዚህ የወንጌል ስራ ማዋል አለብን። ቤተክርስቲያንም ልዩ ትኩረትና በጀት መድባ የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎትን በሰፊው የምትገባበት ጊዜ አሁን ነው።

ቃልኛ :- እንደ አንድ ክርስቲያን እንዲሁም አገልጋይ ስለ ሀገራችን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ምን ትያለሽ?

ህይወት:- ዛሬ ቤተክርስቲያን በአሁን ሰአት ከገባችበት ክፍፍልና እኔነት ወጥታ ወደ አንድነት እና ፍቅር ክርስቶስን ወደ መምሰል እንድትሄድ ሁሉም ቆመው አንድ ወደሚያደርገን ወደ ክርስቶስ ወንጌል መመለስ አለብን። መከሩ ብዙ ስለሆነና ብዙ ስራ ስለሚጠብቀን ወደ ጉዳያችን በሰፊው መምጣት አለብን። መልዕክታችን የሆነውን ክርስቶስን ብቻ መናገርና ማሳየትም አለብን እላለሁ። ብዙዎች ወደ ዘልአለም ሞት እየሄዱ እኛ ግን ካልተሰጠን ርዕስ ወጥተን ክርስቶስን ብቻ ማድመቅ አለብን።ዋናው ነገር ደግሞ የእግዚአብሔርን ድምፅ ብቻ እየሰማንና በርሱ እየተመራን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ቃልኛ :-- እግዚአብሔር ባይኖርሽ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ባይኖርሽ ህይወቴ ምን ይመስል ነበር ብለሽ ታስቢያለሽ? በተለያየ ሁኔታ በሱስ ፤ ከእግዚአብሔር ቤት በመራቅ ፣ በሀጥያት ልምምድ እና ድካም ላሉ ምን ትያለሽ?

ህይወት:- ራሴን ያለጌታ ማየት በጣም ይከብደኛል። ብቻም ሳይሆን ያለመኖር ብዬ ብል ይሻላል። በተለይም የእግዚአብሔርን አብሮነት ህልውናውን ለቀመሰ የእርሱን አባትነት የተረዳ ሰው ያለእርሱ መኖር እጅግ ከባድ ነው። ያለ እርሱ መኖር የእውነት አልችልም እስትንፋሴ ነው። በሱስ ውስጥ በተለያየ የድካምና የሀጥያት ልምምድ ውስጥ ላሉ የምለው ነገር ቢኖር ከዚህ ነገር ሊያወጣ የሚችል ጌታ ስላለ በራሳችን እንደማይሆን አውቀን ሁልጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ወደ ሚወደንና ወደ የሚረዳን ጌታ መቅረብ አለብን። እውነተኛ ደስታና እረፍት ያለው በጌታ ቤት ስለሆነ ከገባንበት ነገር ሊያወጣን ወደ ሚችለውና ሁሉን ነገር በሚያውቅ በጌታ ፊት መሆን ይጠቅማል። ለሰይጣን ከነኬ ጆሮ መስጠት የለብንም። ቀድሞ ያዳነን ጌታ አሁንም ከማንኛውም ነገር ሊያድነን እንደሚችልና እንደሚወደን ማገንዘብ አለብን። እርሱ ሁሌም ሊቀበለን ዝግጁ ነው። ሁሉ ለእርሱ ቀላል ነው። ክብር ለጌታ ይሁን። ሮሜ 8÷1

ቃልኛ :-- በመጨረሻም ይሄን ለሚያነቡ ሰዎች ፤ ወጣቶች ተማሪዎች ክርስቲያን ለሆኑ ላልሆኑ የምታስተላልፊው መልዕክት ካለሽ?

ህይወት:- መልዕክቴ አንድ ነው እርሱም ሰው ሁሉ የሞተለትን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ቢያውቅ ደስ ይለኛል። ወጣቶች ክርስቲያኖች ይሄን የከበረ ጊዜያችሁን ቅድሚያ ለመንፈስቅዱስ ስጡት እርሱ ሁሉ ነገራችሁን እንዲቆጣጠር ፍቀዱለት። በመንፈስቅዱስ ምሪትና መገኘት ውስጥ ኑሩ መወደዳችሁንና የእግዚአብሔርን አባትነትን ሁልጊዜ አስተውሉ። ከምንም ነገር አትነሱም። በትምህርታችሁና በእያንዳንዱ የህይወት አቅጣጫም ቢሆን ስኬታማ ትሆናላችሁ እንጂ እርሱን አስቀድማችሁ ወደ ኋላ አትቀሩም። ጌታ ኢየሱስን የህይወታችሁ ጌታ ላላደረጋችሁ ደግሞ ኢየሱስ ራሱን እስከመስጠት ድረስ አለምን እንደወደደ ቃሉ ይናገራልና ወደርሱ ኑ። ህይወት ማለት ኢየሱስ ብቻ ነው። ኑ ታርፉላችሁ ኢየሱስ ይወዳችኋል ማቴ 11÷28

"...ሰው ሁሉ የሞተለትን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ቢያውቅ ደስ ይለኛል..."

ቃልኛ :- ለአንባብያን ከአዲሱ "አባትነትህ" አልበምሽ እንዲሰሙት የምትጋብዥው ዝማሬ ምረጭልን

ህይወት:- እውነት ለመናገር እኔ ሁሉንም መዝሙሮቼን በጣም ነው የምወዳቸው ለማለት ብቻ ሳይሆን መንፈስቅዱስ ከህይወቴ ያፈለቃቸው ናቸው። "አባትነትህ" አልበም 13 መዝሙሮችን ይዟል በውዳሴ አፕሊኬሽን በነፃ ቀርቧል። ሁሉንም ብትሰሙ ደስ ይለኛል። ግን እሺ Track-8 "ኢየሱስ" የሚለውን መዝሙር። ጌታ ኢየሱስ ለኛ በመስቀል የሆነውን የሚያሳይ ዝማሬ ነው። ይሄን ጋብዣለሁ። ኢየሱስ ጌታ ነው።

ቃልኛ :- ዘማሪት ህይወት መለሰ የመፅሔታችን እንግዳችን ሆነሽ ስለቀረብሽ ጥያቄዎቻችንን ስለመለስሽ እጅግ በጣም እናመሰግናለን። የተባረከ የአገልግሎት ጊዜ እንዲሁም ኑሮ እንዲሆንልሽ እንመኛለን። እግዚአብሔር ያክብርን።

ህይወት :- እኔም የዚህ መፅሔት እንግዳ ስላደረጋችሁኝ ከልቤ አመሰግናለሁ። ጌታ ዘመናችሁን ይባርክ

Mh
GRAPHICS
Feel The Fascination!

## በልዩ ጥራት የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

- ሎጎ ዲዛይን
- የዲጂታል መፅሔት ዲዛይን
- የዝማሬ ፖስተር
- የአልበም ከቨር
- የልደትና ሰርግ ካርዶች
- ቢዝነስ ካርድ
- የባነር ዲዛይን
- የፍላየርና የብሮሸር ዲዛይን
- የቲሸርት ዲዛይን
- የፊልምና የማስታወቂያ ፖስተር
- እና ሌሎች

ይደውሉ (+251) 920019699

በማህበራዊ ገፆች ያግኙን

TELEGRAM @MHGRAPHICS
INSTAGRAM @MHGRAPHICSHD





# ነቢያትና የነቢያት አገልግሎት

በነብይ መሳይ አለማየሁ



## ክፍል-1

### የዚህ አጭር መልእክት አላማ

1-የነቢያት አገልግሎትና የነቢይነት ስጦታ በእግዚአብሔር ቃል እንድንረዳና ከጸጋው ተከፋዮች እንድንሆን እውቀት ማስጨበጥ፣
2-የነቢያት አገልግሎት ለቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገት እና በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ያለውን ሚና መተንተንና ማስተማር፣
3-እውነተኛና ሐሰተኛ ነብያት የምንለይባቸውን መሰረታዊ የሆኑ መመዘኛዎችንና እንዴት እንደምንመዝን ለማስገንዘብ ነው።

### ነቢያትና የነቢያት አገልግሎት

እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:11
●ነብያት በእግዚአብሔር ሉአላዊ ምርጫና ውሳኔ ተጠርተው የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አጀንዳ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ መንፈሳዊ ሰዎች ናቸው።
●በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያንን ውስጥ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገት፣ቅርፅ፣እና ሙላት ይኖራት ዘንድ ከተሰጡት አምስት ስጥታዎች አንዱ ነው።

### የነብይ የስሙ ትርጉም

ነብይ ለሚለው ስም የብሉይ ኪዳን መጻህፍት ሶስት ቃላትን በመለዋወጥ ይጠቀማል። 1ኛ-ሮኢ(Roeh) ባለራእይ ማለት ሲሆን ወደፊት የሚሆነውን አስቀድሞ የሚያይ ማለት ነው።
2ኛ-ኮዜህ(Chozeh)ማለትም በራዕይ የሚያይ የሚመለከት፣የሚያስተውል ማለት ነው። 3ኛ-ነቪይ(Na'bi) እግዚአብሔርን ወክሎ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውጅ ማለት ነው።
●ነብይ ለሚለው ስም አዲስ ኪዳን ፕሮፌት(Prophet )የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል።ትርጉሙም ወደፊት ሊመጣና ሊከሰት ስላለ ነገር አስቀድሞ የሚናገር ማለት ነው። ፕሮፌት(Prophet የሚለው ቃልበብሉይኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ 95ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

●ይህ prophet የሚለው ስም በኤፌሶን 4፡11 መሰረት መንፈሳዊ ለሆነ አላማ ጥቅም ላይ የዋለውን ትርጉም ማለት እንደሆነ ጸሐፊው ልብ ይለዋል።ምክንቱም በወቅቱ ግሪኮች በየትኛውም ዘርፍ አንድን ምሁር/አስተማሪ ሰው ለመግለጽ ፕሮፌት(Prophet) የሚለውን ቃል ይጠቀሙ ነበርና።
●በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 133 ነብያት ተጠቅሰዋል፤ ከነሱም ውስጥ 16ቱ ሴት ነብያት ናቸው።
●በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመጀመርያ ጊዜ የተጠቀሰው ነብይ አባታችን አብርሃም ነው። ''አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ፤ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ። ( ዘፍጥረት 20:7)
●እንዲሁም ነብያት ሳይሆኑ ትንቢት የተናገሩ ከ70 ሰዎች በላይ ነበሩ።ከነሱም ውስጥ የእስራኤል ሽማግሌዎች፣ንጉስ ሳኦል፣ሌpሎችም ነበሩ። '' እግዚአብሔር በደመናው ወረደ፥ ተናገረውም፥ በእርሱም ላይ ከነበረው መንፈስ ወስዶ በሰባው ሽማግሌዎች ላይ አደረገ፤ መን ፈሱም በላያቸው ባደረ ጊዜ ትንቢት ተናገሩ፤ ከዚያ በኋል ግን አልተናገሩ ም።''''ኦሪት ዘኍልቍ 11:25

## የእውነተኛ ነብያት እና ሐሰተኛ ነብያት መገለጫዎች

► ከእግዚአብሔር የሆነ ድምጽና በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመሰረታዊ አስተምህሮቶች ላይ መሰረት ያደረገ ትንቢት ይናገራሉ።
► ታላቁን ተልእኮ ማእከል ያደረገ አገልግሎት ያገለግላሉ።
► የተናገሩት ትንቢት ይፈጸማል።
► ክርስቶስን ማእከል ያደረገ አስተምሆሮ ይከተላሉ።
► ሰዎች በአገልግሎታቸው ይታነጻሉ፣ይመከራሉ፣ይጽናናሉ።
► ሰዎችን ለጽድቅ መንገድ ያቀናሉ። ፔጁን ላይክ አድርገው በተከታታይ ትምህርቶች ይባረኩ። ሁለተኛ ክፍል ነብያትና የነብያት አገልግሎት
► እውነተኛ ነብያት እንደ እውነተኛ አገልጋይ ስለ ወንጌል ብለው መከራን የሚቀበሉና በየትኛውም ጎዳና አቋም ይዘው የሚያገለግሉ ናቸው።
''የሚያልም ነቢይ ሕልምን ይናገር፤ ቃሌም ያለበት ቃሌን በእውነት ይናገር። ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አለው? በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፥ ድንጋዩንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር።'' ት. ኤር 23 :28- 29 ''በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ። እኔም። ወዮ ጌታ እግዚአብሔር ፥ እነሆ፥ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ። ወደምሰድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና፥ የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና። ብላቴና ነኝ አትበል።እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር። ትንቢተ ኤርምያስ 1 : 5-8 ''ስለ ሰላም የተናገረ ነቢይ፥ የነቢዩ ቃል በሆነ ጊዜ፥ እግዚአብሔር በእውነት የሰደደው ነቢይ እንደ ሆነ ይታወቃል። ት.ኤርምያስ 28 : 9

## #ሐሰተኛ ነብይ ማለት

► ከላይ እንደተጠቀሰው የእውነተኞቹ ነብያት ተቃራኒ ናቸው።
► ሲቀባም ከእግዚአብሔር ያልተቀባ።
► በሰይጣን መንፈስ የተቀባ።
► የእግዚአብሔርን ቃል የማይቀበል።
► ህዝብን ወደ ጠማማ መንገድ ዘወር የሚያደርግ ነው።
► ሰዎችን በወደቀ ጥበብና በአጋንንት እውቀት ላይ የተመሰረተ ነው።

እነሆ፥ ከምላሳቸው ትንቢትን አውጥተው። እርሱ ይላል በሚሉ ነቢያት ላይ ነኝ፥ ይላል እግዚአብሔር። ''ት. ኤር 23 : 31
''እነሆ፥ ሐሰትን በሚያልሙ በሚናገሩም በሐሰታቸውና በድፍረታቸውም ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ፥ ይላል እግዚአብሔር፤ እኔም አልላክኋቸውም አላዘዝኋቸውምም ለእነዚህም ሕዝብ በማናቸውም አይረቡአቸውም፥ ይላል እግዚአብሔር።'' ት.ኤር 23 : 32 ''

ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፥ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፥ ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፥ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፥ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ፤ በፍጻሜውስ ምን ታደርጋላችሁ ኤር5:31

●ነብያት ለአይምሮ ልንረዳ የማንችላቸውን ነገሮች፣የማይመረመር፣ድንቅና ተአምራቶች እና ልምምዶች ነበራቸው። ነገር ግን ይህ ሁሉ አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ኪዳን ላይ የተመሰረተ እና ህጉን ማእከል ያደረገ ነበር።አላማቸው የግል ጥቅም ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምና ማስፈጸም ነው።
●የነብያት አገልግሎት በቀጥታ መንፈስቅዱስ መራሽ አገልግሎት ነው። መንፈስቅዱስ ወደ መንፈሳቸው ያመጣውን መልእክት ለግለሰብ፣ ለቡድኖች፣ለሃገር ወዘተ ይናገራሉ።
●የነብያትን አገልግሎት በጥንቃቄ ካላጤንነው የማይገባን፣በራስ ሚዛን በመመራመር የማንረዳው ለአይምሮ ሞኝነት የሚመስሉ ብዙ ነገሮች አሉት። የነብያትን አገልግሎት በእግዚአብሔር ቃሉ ጥልቅ መረዳት እንጂ በላብራቶሪ ፍተሻ አደርጋለሁ ብሎ ማሰብ ትልቅ የሞኝነት መገለጫ ነው።
●የነብይ አንዱ አገልግሎት ትንቢት መናገር ነው፤ትንቢት ደግሞ ወደ ነብዩ የሚመጣ ቅጽበታዊ መገለጥ ነው።ነብይ ለመተንበይ አጥንቶ፣አንብቦ፣ አስቦ አሰላስሎ መጽሐፍትን አገላብጦ ሌክቸር እንሚሰጥ አስተማሪ ሆኖ ሳይሆን መንፈስቅዱስ ድንገት የሚሰጠውን መልእክት ነው የሚናገረው። መልእክቱ ለነብዩ የውስጥ አይን የሚታይ፣በውስጥ ጆሮ የሚሰማ፣ በውስጥ ምላስ የሚቀመስ፣በወስጥ እጅ የሚዳሰስ ሆኖ ይመጣል።ይህ ማለት የሰው ልጅ በአምስቱ ህዋሳት(sense organs) አማካኝነት ነገሮችን መቅመስ ፣ማሽተት፣ መዳሰስ፣መስማትና ማየት እንደሚችለው ሁሉ ነብያትም በመንፈስ ነገሮችን ይለያሉ።

እግዚአብሔር በእኛ አይምሮ ሊደረስባቸው የማይችሉ እልፍ አእላፍ ስራዎችን ሰርቷል፣እየሰራም ነው፣ወደፊትም ይሰራል።አብዛኛውን ስራውን ደግሞ የሚሰራው በመረጣቸው ባርያዎቹና ህዝብ አድርጎ በዋጃቸው ገንዘቦቹ ነው።በክርስቶስ ለሆንን ዛሬም በእኔ እና በእናንተ ታላቅ ስራ መስራት ይችላል። የእግዚአብሔር ገንዘቦች ውስጥ ነብያት ይገኛሉ። ነብያትም የእግዚአብሔር መጠቀምያ ሸክላዎች ስለሆኑ በታሪክ ውስጥ በመጽሐፍቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር አጀንዳ በነሱ ሲፈጸም አይተናል። ለምሳሌ በብሉይኪዳን ዘመን የነቢያት አገልግሎትና አብዛኛው አሜን ብለን አምነን ከመቀበል ውጪ በራስ ጭንቅላት መርምረን የማንተነትናቸው በእምነታቸውና በቅባታቸው ታላላቅ የጌታን ስራ ሰርተው አልፈዋል።

በብሉይ ኪዳን የነብያት አገልግሎት ከካህናት አገልግሎትና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር አንድ አይነት ሳይሆን የተለየ አገልግሎት ነበር። አገልግሎቱ የራሱ የሆነ አሰራር፣ባህሪ፣ ተአምራዊ ውበት ያለው አገልግሎት ነው። በብሉይ ዘመን የነበረውን የነብያት አገልግሎት ስንመለከት አስተምህሯዋቸውና አላማቸው
የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔርን ማገልገል፣ ህጉን ማስተማርና መለኮታዊ ምሪት መስጠት፣
ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው አካላዊ ፣አይምራዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎት መተንበይና ተአምራቶችን መስራት፣ህዝቡን መምከር፣መገሰጽና ህጉን ማስጠበቅ፣ስለ መጻኢ ዘመን(ስለሚመጣው ዘመን)አስቀድሞ መናገር
የሐዲስ ኪዳን ዘመንንና ስለ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መምጣት፣እና በዘመን መጨረሻዎች ሊሆኑ ስላሉ ክስተቶች ተናግረዋል።

●በብሉይ ዘመን ነብያት ለመፈወስ፣ተአምራት ለማድረግ፣ገንዘብ ለመባረክ፣እህልና ውሃን ለመባረክ፣የተዘጋ ማህፀን መክፈት፣ልጅ ለሌላቸው ልጅ እንዲወልዱ መጸለይና መተንበይ ስራቸው ነበር።
ለምሳሌ የኤልሳን አገልግሎት በጥቂቱ እንመልከት ⬇..እርሱም። አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ፥ ጨውም ጨምሩበት አለ፤ ያንንም አመጡለት። ውኃው ወዳለበቱም ምንጭ ወጥቶ ጨው ጣለበትና። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ፤ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይሆንበትም አለ። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 2:20- 20
እርሱም። በሚመጣው ዓመት በዚህ ወራት ወንድ ልጅ ትታቀፊአለሽ አለ፤ እርስዋም። አይደለም ጌታዬ፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ባሪያህን እንዳትዋሻት እለምንሃለሁ አለች።ሴቲቱም ፀነሰች፥ በዚያም ወራት በአዲሱ ዓመት ኤልሳዕ እንዳላት ወንድ ልጅ ወለደች። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 4: 16-17እንዲህም አለ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በዚህ ሸለቆ ሁሉ ጕድጓድ ቆፈሩ። እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። ነፋስ አታዩም፥ ዝናብም አታዩም፥ ይህ ሸለቆ ግን ውኃ ይሞላል፤ እናንተም ከብቶቻችሁም እንስሶቻችሁም ትጠጣላችሁ። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 3: 16- 17
ንዕማንም በፈረሱና በሰረገላው መጣ፥ በኤልሳዕም ቤት ደጃፍ ውጭ ቆመ። ኤልሳዕም። ሂድ፥ በዮርዳኖስም ሰባት ጊዜ ታጠብ፤ ሥጋህም ይፈወሳል፥ አንተም ንጹሕ ትሆናለህ ብሎ ወደ እርሱ መልእክተኛ ላከ።ንዕማን ግን ተቈጥቶ ሄደ፥ እንዲህም አለ። እነሆ፥ ወደ እኔ የሚመጣ፥ ቆሞም የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ፥ የለምጹንም ስፍራ በእጁ ዳስሶ የሚፈውሰኝ መስሎኝ ነበር።መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 5:9- 11

## ሜጀር ፕሮፌት እና ማይነር ፕሮፌት?

ይህ አገላለጽ የመጣው የብሉይ ኪዳንን የነብያት መጽሐፍት ስናጠና ግልጽ እንዲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ለሁለት ከፍሎ ለማየት የመጣ ስያሜ ነው።
ሜጀር የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ብዛት ያለው ማለት ነው፤የቃሉ አገባብ አለቃነትን ለመግለፅ አልዋለም::
ሜጀር ፕሮፌት የሚባሉት እነ ነብዩ ኢሳያስ፣ኤርምያስ፣ሰቆቃወ ኤርምያስ ፣ህዝቅኤል፣ዳንኤል፣ማይነር ፕሮፌት የሚባሉት ደግሞ ሆሴዕ፣ኢዩኤል፣ ሚኪያስ፣ዮናስ፣አብድዩ፣አሞፅ፣
ሶፎኒያስ፣ሃጌ፣ዘካርያስ፣ሚልኪያስ የሚባሉት ነብያቶች ናቸው።
●ሜጀር ፕሮፌት የተባሉት የጻፏቸው የትንቢት መጻህፍት ረጅምና ሰፋ ያለ ጥልቅ ይዘት ስላለው ነው።
●ማይነር ፕሮፌት የተባሉት የጻፏቸው የትንቢት መጻህፍት አጠር ያለ አነስ ያለ ይዘት ያላቸው ስለሆኑ ነው።
ሜጀር ፕሮፌት እና ማይነር ፕርፌት ብለው የተከፋፈሉት የነብያትን መጽሐፍት ስናጠና እንዲረዳን ነው።ሜጀር ፕሮፌት እና ማይነር ፕሮፌት የጻፏቸ ው መጽሐፍት ላይ የተመሰረተ የተሰ ጠ ስያሜ ነው።ማይነር ፕሮፌት የሚባሉት መገለጣቸውና ትንቢታ ቸው ማይነር ሆኖ አይደለም። ሁለቱ ም እኩል የሆነ መለኮታዊ አገልግሎት ነበራቸው፣መለኮታዊ ድምጽ ተከትለው ጽፈዋል።ሁለቱን ከፍሎ ለማየት የተፈለገው በቀላሉ 17 የነብያት መጽሐፍት ስናጠና ለይቶ ለማወቅ እንጂ ለማበላለጥ አይደለም።ባለማወቅም እያወቁም ብስል ያልሆኑ አንዳንድ ጥቂት ነብያት ግን ሜጄር ዋን(Major One) እያሉ ራሳቸውን ሰይመው እናያለን። ምናልባት የሜጀር አሰያየም ከየት እንደመጣ ከተረዳችሁ በኋላ ሜጀር መባሉ ሌላ የቅባት ደረጃ እንዳልሆነ ስለምትረዱ ሜጀር ተብሎ መጠራቱ እንደማያስፈልግ ትረዳላችሁ።
በዚህ ዘመን ሜጀር የሚለውን ሰዎች በሌሎች ላይ ለመሰልጠን ይጠቀሙ በታል።የበላይነት ሚስጥር ዝቅ ማለት ነው። '' ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤
እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።ማቴ 20:27-28 በዚህ ዘመን ማንም ነብይ ሜጀር ተብሎ ሊጠራ አይገባውም።

ሜጀር ዋን ተብሎ የምንሰማው ስያሜ ያለቦታው የገባ ነው።
●ሜጀር ዋን መባል ክብር አይደለም! ምንም አይጨምርም ምንም አይቀንስም።
●ትህትና የእውነተኛ ነብያት መገለ ጫ ነው።
●ነቢይ ሆይ ከትዕቢት ተጠንቀቅ! ትዕቢት እንደ ሚበቅል ዘር ነው።ዘር ደግም ይበቅላል፤ያድጋል ከዛም ይጠቅማል ወይም ይጎዳል።
●ነብይ ሆይ የህይወት ጥራትህን ጠብቅ።ትንቢት የመናገር ስጦታ እና ነብይነት ትንቢት ተናጋሪ ሁሉ ነብይ አይደለም። ትንቢት የመናገር ስጦታ እና ነብይነት የተለያዩ አይነት ስጦታዎች ነው።
መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል :-
ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤1ቆሮ 12 : 10
እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ኤፌ4 : 11

## ትንቢት የመናገር ስጦታ

ትንቢት መናገር ማለት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚሄድ የእግዚአብሔርን ሉአላዊ ሃሳብ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ማወጅ/ መናገር ነው።ትንቢት መናገር እግዚአብሔር እንድናደርገው በቃሉ ያዘዘውን ነገሮች ለሰዎች ማወጅ/ መናገር ነው። ትንቢት የመናገር ስጦታ ያለው ሰው ሰውን ለማነጽና፤ለመምከር፣ ለማጽናናት ነው የሚናገረው። ''ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል። በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።''1ቆሮ14 :3

በነብያትና በትንቢት አገልግሎት ዙርያ ሰፊ ክርክር አለ፤የነብያት ኣገልግሎ በዚህ ዘመን እንደሌለ የሚናገሩ ሰዎች አሉ የሚያነሱትም መከራከርያ ሃሳብ ሐዋርያት ሲሞቱና መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ተጽፎ ሲጠናቀቅ ከዘመናት በፊት አቁሟል ይላሉ።
●ትንቢት/ነብያትም የሉም ለሚሉ ሰዎች የክርክር መሰረት ትንቢት ከመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን ጋር እኩል ስልጣን አለው በሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ነው። በርግጥ ይህ ሃሳብ ልክ አይደለም የነብያት አገልግሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን ጋር ማወዳደር ማሰቡም ስህተት ነው።
● ትንቢት ከመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን ያነሰ እንጂ እኩል ስልጣን የለውም። ሁላችንም ከመጽሐፍ ቅዱስ በታች ነን፣መጽሐፍ ቅዱስ ይገዛናል እንጂ አንገዛውም፤ይመራናል እንጂ አንመራውም፣ የምንናገረው ትንቢት በመጽሐፍ ቅዱስ ይመረመራል፣የማይመረመር ትንቢት የለም፣ ሌሎች ወገኖች ደግሞ የትንቢት ስጦታ በዚህም ዘመን አለ ይላሉ ለመኖሩ የሚያነሱት ማስረጃ ዎች ብዙ ናቸው። ''አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹ ም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ''ኤፌ4 : 11
●የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ሁለተኛው ወገን ነው በትንቢትና በነብያት አገልግሎት መኖር አምናለሁ እኔም ራሴ ጥሪዬ ነብይነት ነው። በመቀጠል መረዳት ያለብን እውነት:- ትንቢት አሁን የተወሰነ ፍላጎትን ያሟላል ይህን የሚያደርገው ግን በከፊል ነው።ፍጹም የሆነው ሲመጣ ያ አገልግሎት በሌላ በላቀ ሁኔታ ፍጻሜ ላይ ይደርሳል ትንቢት ይቆማል፣ ምክንያቱም ጊዜ ያለፈበት ጥቅም የለሽ ይደረጋልና።
'''ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል።1ቆሮ 13 : 9-10 በርግጥ ትንቢት ብቻ ሳይሆን ሌሎቹ ም የአገልግሎት ስጦታዎች ይሻራሉ ።ይሻራል የሚለው የግሪክ ቃል ካታርጊዮ (catargio) ይለዋል። ትርጉሙም የአገልግሎት ጊዜ ማብቂያ ነው።ፍጹም የሆነ የሚለውን ኢክ መረስ (ek merous) ነው። የማይሻር ዘላለማዊ ማለት ነው። ሌላው ማወቅ ያለብን ትንቢትና የነብያት አገልገሎት ከሌሎች ስጦታዎች ይልቅ አላግባብ ለመጠቀም የተመቸ መሆኑን ነው።

**...ይቀጥላል**

# መፅሐፍ-ቅዱስ


## ስለ ጅንጀና (Flirting) ምን ይላል?



**በ አድነው ተመስገን**

በጌታ የሆነ ሰው መጀናጀን አለበት ወይስ ይህ ድርጊት ፈፅሞ መቆም ያለበት ጉዳይ ነው? እንደው ተጀናጅናችሁ የምታውቁ. . . የእናንተ መንገድ እንዴት ነበር ጌታንስ ደስ የሚያሰኝ ነው?

እነዚህን እና ሌሎች በክርስቲያኑ ዘንድ መመለስ ያለባቸውን ነጥቦች አብረን እናያለን። ዛሬ የምንዳስሰው ብዙ ጊዜ ለመንካት የምንፈራውን ብሎም ሐጢያት ስለሚመስለን ጉዳይ ነው መጀናጀን(flirting)።
በመጀመርያ ግን ጅንጀና(flirting) ምንድነው የሚለውን ከአንዳንድ ዲክሽኔሪዎች እንይ። [በእውነቱ በአመርኛ ፍቺውን ለመፈለግ በጣም ሞክሬ ያገኘሁትን የእንግሊዝኛ ፍቺ እንደ ግብዓት ተጠቅምያለው።]
meriam webster dictionary ጅንጀናን እንዲህ ይገልጸዋል።
"Merriam-Webster Dictionary defines “flirt” as a verb which means, “To behave amorously without serious intent. To show superficial interest or liking.” " ጅንጀና ማለት አንድን ሰው እንደማረከን እና እንደወደድነው ለማሳወቅ የምንጠቀመው የውሸት ወይም የማስመሰል ድርጊት ነው።"
"Another definition reads, 'To behave as though attracted to or trying to attract someone, but for amusement rather than with serious intentions.' "
"ወይም የአንድን ሰው ትኩረት ለመሳብ ያን ሰው በውሸት የማስገረም ተግባር ነው።" According to dictionary.com, “flirting” is “making playfully romantic or sexual overtures.”
በቃ በአጭሩ ወሲባዊ ጨወታ ነው ይላል dictionary.com መፅሐፍ ቅዱስ ላይም መጥፎነቱን ለማስየት የተጠቀሰ ክፍል አለ። ( ምሳ 6፡24-25 )



" ከክፉ ሴት ትጠብቅህ ዘንድ፥ ከሌላይቱም ሴት ምላስ ጥፍጥነት።
ውበትዋን በልብህ አትመኘው፤ ሽፋሽፍትዋም አያጥምድህ።" ይህ ትክክለኛው የጅንጀና ምንነት ከሆነ ክርስቲያን የሆነ ሰው ተቃራኒ ፆታ ለመሳብ ፈፅሞ መጠቀም የለበትም። (ችግሩ ግን እየተጀናጀንን ነው ስለዚህ ይህ ጉዳይ መወራት አለበት)
በተለይ ይህን ጊዜ ምክንያት በማድረግ ብዙ ሰዎች Chat ላይ ስለሚያሳልፉ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ምላሰ ጥፍጥናቸውን እየተጠቀሙ ነው። የዚህ መልዕክት አላልማም ይህን ድርጊት በተገቢው መንገድ እንዲከወን ማድረግ ነው። አንድ ክርስቲያን አንድን ሰው መውደዱን ወይም ስሜት እንዳለው ግልፅ ነው በምን አይነት መንገድ ነው ፍላጎቱ የሚገልፀው ቢለያይም ማለት ነው።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያን ወጣቶች አንድን ሰው ሲወዱ እና የወደዱት ሰው ግን ምንም አይነት አፀፋ ካልመለሰ ሁለት ነገሮችን ነው የሚያደርጉት።
1. የመጀመርያው ዝም ማለት ብዙ መፀለይ እና ተስፋ ማድረግ
2. ሁለተኛው በጣም ገፍተን ከሔድን ደግሞ የልባችንን ስሜት በድፍረት በመግለጽ የሚመጣውን መቀበል።
ሌላው ግን ከሁለቱም የሚጠቀሙ ትንሽ የምላስ ጥፍጥነት(ጅንጀና) ጌታን የማያሳዝን በመጠቀም ፍላጎታቸውን የሚያሳዩ አሉ። (አልዋሻችሁም እንደ እኔ ይህ የተሻለ ይመስለኛል በትክክለኛው መንገድ ለዛ ሰው ፍላጎት እንዳለን ማሳየት)

## ለምንድነው የምትጀናጀኑት?

- የምላስ ጥፍጥናችሁን የምትጠቀሙበት ዋናው አላማ ምንድነው አንድን ሰው ላማሳት እና ለጊዚያዊ ስሜት ነው? እንደዛ ከሆነ መጀናጀን የራሱ የሆነ ሳቢ ነገር ቢኖረውም ግዴታ ማቆም አለባችሁ። ነገር ግን እውነተኛ ስሜታችሁን ለመግለፅ ፈልጋችሁ ነው የምትጠቀሙት? እንደዛ ከሆነ መፅሀፍ ቅዱስ ስለ መጀናጀን ምን እንደሚል አብረን እንይና እንዴት ቅዱሱን መንፈስ ሳናሳዝን እንደምንጠቀመው እናንተ ወስኑ።

## መፅሐፍ ቅዱስ ስለመጀናጀን ምን ይላል?

አሁን የብቸኝነት ህይወት ውስጥ ናችሁ?
ወደ ፊት ባል ይሆነኛል ወይም ሚስቴ ትሆነኛለች የምትላትን ሴት ነገር ግን ያን ሰው ወይም ያቺን ሴት ለእናንተ ያለውን ወይም ያላትን  ስሜት ማወቅ ቢያቅታችሁ ምንድነው የምታደርጉት?
ስለዛ ጉዳይ መፆምና መፀለይ?
ወይስ እርግፍ አድርጋችሁ ትተዋላችሁ?
ወይስ በአንድ ጊዜ የልባችሁን ስሜት ዝርግፍ አድርጋችሁ መናገር?
ወይስ በጣም ረዥም ደብዳቤ ፅፋችሁ ስለ ስሜታችሁ ማሳወቅ?

እውነት ነው መፆምና መፀለይ ምንም ክፋት የለውም ግን ስሜታችሁን ያን ሰው እንዲያውቅ ላያደርግ ይችላል። (ተረዱኝ በሆነ መንገድ ያ ሰው ማወቅ አለበት ፀሎቱ እንዳለ ሆኖ)
እርግፍ አድርጎ መተው ደግሞ መልካም ሰው ሊያሳጣችሁ ይችላል በዛው ልክ ደግሞ ስሜታችሁን ዘርግፋችሁ ማውራቱ ያ ሰው ለእናንተ ያለውን አመለካከት ሊቀይር ይችላል። ምንም የማትቀርቡት አይነት ሰው ከሆነ ምን ያክል ሊከብድ እንደሚችል አስቡት የተወሰነ ጓደኝነት እና መቀራረብ እንኳን ቢኖር እንደ ዱብዳ ስሜታችሁ ለዛ ሰው መግለፁ ግንኙነታችሁን ሊያሻክረው ይችላል።

መፅሀፍ ቅዱስ ስለ መጀናጀን ወይም flirting ቀጥታ እንዲህ እንዲህ ብሎ ባይናገርም ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ትዕዛዝ እና መርህ ውስጣችን የሚቀር ነገር ይኖራል ብዬ አስባለው። በጣም ማስተዋል ያለብን ምንም ነገር ለማድረግ ስንነሳሳ ምክንያታችንን ጠንቅቀን ማወቅ አለብን ምክንያቱም የተነሳሳንበትን አላማ ካወቅን ላድርግ ወይስ አላድርግ የሚለውን ጥያቄ መመለስ እንችላለን። ስለዚህ ስለ flirting ስናስብ ለምንድነው የምናደርገው ብለን መጠየቅ አለብን።

## ቀጥሎ ለምጠቅሰቸው ምክንያቶች ፈፅሞ አትጀናጀኑ. . .

- በራስ መተማመንን ለማሳደግ
- ጥሩ ስሜት እንዲሰማችሁ ብላችሁ
- ጓደኞቻችሁ ስለእናንተ ጥሩ ነገር እንዲያስቡ ለማድረግ
- ለስጋዊ ፍላጎታችሁን ለማርካት

እነዚህን እና ሌሎች በጣም ብዙ መጥፎ ምክንያቶችን መዘርዘር እንችላለን። ነገር ግን የልባችሁ መነሳሳት ለመልካም ከሆነ እና ሌሎችን የማያሰናክል ከሆነ እናንተ ወዳችሁት ነገር ግን ያ ሰው ለእናንተ ያለውን ስሜት ለማወቅ በጥቅቂቱ ምላሰ ጥፍጥናችሁን ብትጠቀሙ መልካም ይመስለኛል።

መፅሐፍ ቅዱስ ማቴ. 18፡6-7 እንዲህ ይላል።
" በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።
ወዮ ለዓለም ስለ ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።" እዚህ ክፍል ላይ ሰው ማሰናከል ምን ያክል የከፋ ተግባር እና እግዚአብሔርንም የሚያስቆጣ ያሳያል። በክርስትና ህይወታችን የትኛውንም አይነት ትግባር ከመቸፀማችን በፊት የቱንም ያህል እኛ ብናምንበትም ሰው ያሰናክላል አያሰናክልም ብለን ራሳችንን መጠየቁ እጅግ የተሻለ ነው። በጣም እንድታስተውሉ እና በተሳሳተ አቅጣጫ እንዳትረዱ የምፈልገው ከላይ ያወራኋቸውን እና ቀጥሎ የማወራቸውን ነገሮች ከማድረጋችሁ ጊዜዬ ነው ወይ ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ። የትዳር ምዕራፍ ለመጀመር ሰው መርጣችሁ ያ ሰው ለእናንተ ምንም አይነት ምላሽ ካልሰጠ ብቻ ለዛ ሰው ያላችሁን ስሜት በልበ ብሩህነት ለመግለፅ ሞክሩ። ያለጊዜያችሁ ግን የምትጀናጀኑ ከሆነ እመኑኝ የልባችሁ መሻት ሌላ ነው ሰው እያሰናከላችሁም ጭምር ነው።ስለዚህ አስተውሉ።

ይህ ልጅ ግን ጤነኛ ነው እንዴት አድርጌ ነው ስሜቴን በብሩህ ልብ ቀስ አድርጌ መግለፅ የምችለው ልትሉ ትችላላችሁ። ለዚህ የሩትን ታሪክ መፅሐፈ ሩት ምዕራፍ 3 ላይ እንመልከት።

## መጽሐፈ ሩት 3፡1-10

" አማትዋም ኑኃሚን አለቻት፡- ልጄ ሆይ፥ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍት አልፈልግልሽምን?
አሁንም ከገረዶቹ ጋር የነበርሽበት ቦዔዝ ዘመዳችን አይደለምን? እነሆ፥ እርሱ በዛሬ ሌሊት በአውድማው ላይ ገብሱን በመንሽ ይበትናል።
እንግዲህ ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽን ተላበሺ፥ ወደ አውድማውም ውረጂ፤ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ ለሰውዮው አትታዪው።
በተኛም ጊዜ የሚተኛበትን ስፍራ ተመልከቺ፥ ገብተሽም እግሩን ግለጪ፥ ተጋደሚም፤ የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል።
ሩትም፡- የተናገርሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ አለቻት።
ወደ አውድማውም ወረደች፥ አማትዋም ያዘዘቻትን ሁሉ አደረገች።
ቦዔዝም ከበላና ከጠጣ ሰውነቱንም ደስ ካሰኘ በኋላ፥ በእህሉ ክምር አጠገብ ሊተኛ ሄደ፤ ሩትም በቀስታ መጣች፥ እግሩንም ገልጣ ተኛች።
መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ጊዜ ሰውዮው ደነገጠ፥ ዘወርም አለ፤ እነሆም፥ አንዲት ሴት በእግርጌው ተኝታ ነበረች።
እርሱም፡- ማን ነሽ? አለ። እርስዋም፡- እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ፤ ዋርሳዬ ነህና ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ አለችው።
ቦዔዝም አላት፡- ልጄ ሆይ፥ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ፤ ባለጠጋም ድሀም ብለሽ ጐበዛዝትን አልተከተልሽምና ከፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ጊዜ ቸርነት አድርገሻል።"

## ከማን ጋር ነው የምትጀናጀኑት?

መፅሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ጅንጀና ጌታን ሳናሳዝን ለትክክለኛው ሰው እውነተኛውን ስሜት ለመግለፅ ከማን ጋር ነው የምጀናጀነው የሚለውን ማወቁ መልካም ነው። ከባለትዳር ጋር? ፣ከሌላ ሰው ጋር? በእጮኝነት ህይወት ውስጥ ካለ ሰው?፣ ለማግባት የማትፈልጉትን ሰው ከጀነጀናችሁ ሀጥያት እየሰራችሁ እንደሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ።

መፅሐፍ ቅዱስ ከማያምን ጋር እንዳንጣመር ግልፅ አድርጎ ያስቀምጣል ስለዚህ ወደፊት በትዳር ህይወታችሁም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወታችሁ ሰላም ሊያሳጣችሁ ከሚችል ነገር ፈፅሞ አትሞክሩ።
( 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6፡14)
"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?" ሌላው በአንድ ጊዜ ከአንድ ሰው በላይ ጋር እየተጀናጀናችሁ ከሆነ ቶሎ ብታቆሙ መልካም ነው ምክንያቱም በዚህ ጊዜ አላማችሁ ትዳር ሳይሆን በመጀናጀን ሂደት ውስጥ ያለን ደስታን ፍለጋ ይመስለኛል።

## እንዴት ነው የምትጀናጀኑት?

አሁን ይህን ርዕስ ይዤ ወደመጣሁበት ዋና ጉዳይ ደርሰናል እንዴት መጀናጀን አለብን?

### 1. መመኘት ሐጥያት እንደሆነ በማወቅ።

( የማቴዎስ ወንጌል 5፡27-29)
"አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።
ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና።"

### 2. ራሳችሁን በመግዛት

( ቲቶ 2፡6-8)
"ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው።
የሚቃወም ሰው ስለ እኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር፥ በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ፤ በትምህርትህም ደኅንነትን፥ ጭምትነትን፥ ጤናማና የማይነቀፍ ንግግርን ግለጥ።"

### 3. ኢሳያስ ምዕራፍ 3 ላይ እንደተገለፁ አይነት ሴቶች ባህርይ ባለመያዝ

( ኢሳ 3፡16-17)
"ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- የጽዮን ቈነጃጅት ኰርተዋልና፥ አንገታቸውንም እያሰገጉ በዓይናቸውም እያጣቀሱ፥ ፈንጠርም እያሉ፥ በእግራቸውም እያቃጨሉ ይሄዳሉና
ስለዚህ ጌታ የጽዮንን ቈነጃጅት አናት በቡሀነት ይመታል፥ እግዚአብሔርም ኅፍረተ ሥጋቸውን ይገልጣል።"
ስለዚህ ሆን ብላችሁ በየአደባባዩ የትውልድን አይን እየተጣራችሁ አታሰናክሉ ጌታን ያስቆጣል።

### 4. በውበት ስለተማረካችሁ ብቻ ባለማድረግ

(ምሳሌ 31፡30 )" ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች።" ሳጠቃልል ከነፍሳችሁ ያፈቀራችሁትን ሰው እንጂ ፈፅሞ ለውሸት ስሜት ብላችሁ ጥፍጠ ምላሳችሁን አትጠቀሙ። ( 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3፡4-4 )
"ለእናንተም ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥
ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።"

*********

# ትንቢታዊ ጋብቻ?

## ምነው ትቢያ ሆነሳ?

**በቢንያም አዲሱ**



(ከሄለኣም በፀሐፊው ተደርሶ (ቢኒያም አዲሱ) ለህትመት እየተዘጋጀ ካለ መፅሐፍ የተቀነጨበ)

ጋብቻ በሁለት ተቃራኒ ፆታ ባላቸው ጥንዶች መልካም ፈቃድ የሚፈፀም ሲሆን የመሠረተው እግዚአብሔር ነው። የዚህ ህይወት ጀማሪወች ኣዳምና ሄዋን ሲሆኑ በሁለቱ ጥምረት መካከል እግዚአብሔር ለአለም ሁሉ የሚሆን የተቀደሰ ተግባር ዓላማ ክቡርነት እና ሰወች በጥንቃቄ መጠበቅ እዳለባቸው ያስተምራል[ሚል2:15-16፡ ዕብ 13:1-2]ታዲያ "ሀገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው" እንዲሉ አበው የጋብቻ ምንነት ፣ትዳርን የተሳካ ለማድረግ እንድትችል የሚረዱህ አስር መርሆች ፣በትዳር ውስጥ ማድረግ የሌለብህ ጉዳዮች እያልኩ ነፍስህን ላዝላት አልሻም አስብልሃለሁ እና ደግሞ ብናገርስ! የምን ላይ ታች ነው? እውነት እውነቱን እናውራ እንጂ በፍቅር እንግለጥ ያወቅነው ሳንገልጥ" የጋን ሙብራት" አንሁን። ስለ ምን? ስለትንቢታዊ ጋብቻ ነዋ!! በዚህ ጉዳይ ብዙ ሰዎች በተለያዬ መንገድ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ በተለይ ይህ ስጦታ በጥንቃቄ እግዚአብሔርን በመፍራት እስከ መጨረሻው በፍቅር እና በእውነተኛ መንፈሳዊነት መኖር አለበት ብለው የሚያምኑ ወንጌላውያን ክርስትያኞች ዘንድ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።በዚህ ዘመን ጊዜው የሚጠይቀውን መረዳት በመያዝየጋብቻ መልካምነት ሊገለጥ ይገባል።

አንባቢ ሆይ የዚህ ፅሑፍ ዓላማ የክርስቶስ ትምህርትበማስተማርና የመንፈስን ሃይል በመግለጥ የሚተጉ ውድ አገልጋዬችን በመካድ ፍልስፍናዊ ካባ አልብሰን አገልግሎትን!ለማንኳሰስ ሳይሆን መናኛ የሆነ መልዕክት ማለትም:- በእግዚአብሔር ቃል በእኛ ውስጥ ባለ በጎ ህሌና (መንፈስ ይህም ከእግዚአብሔር ነው ፤ "የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው የሆዱን ጉርዶች ሁሉ የሚመረምር")፣ ከተፈጥሮ እውነት ፍፁም ተቃራኒ ሆነው የሚመጡ ሰዋዊ መረዳቶች በመንፈሳዊነት ሰበብ የሰውን ህይወት እንደ ቅንቅን የበሉ የተፀነሰን ልጅ ማህፀን ውስጥ ያፈኑ ፣የቆመን ያስቀመጡ፣የሚሮጥን ያዘገዩ ብዙ ኢ-መፅሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶች በስፋት በመኖራቸው ደጉ ያገሬ ህዝብ ቅቤ ነው ብሎ የሸመተው ሙዝ ፤ ማር ነው ብሎ ያሰበው ስኳር እየሆነበት እንደተቸገረው ሁሉ መልካም ነው። ብሎ የተቀበለው አፋዊ ንግርት ከተባለው በተቃራኒ እየሆነ ለሰው እንዳይነገር ሀፍረት እግዚአብሔርን እንዳይጠይቅ አለማመኔን ይኮንነዋል በማለት ፍፁም የመጠየቅ የነፃነቱን በነፃ ተቀብለውት እስረኛ ሆኗል።

ትንቢታዊ ጋብቻ ምነው ትቢያ ሆነሳ !!! ትንቢት እና ያስከተለው መዘዝ ብዬ በጣም ውስጤ ያለ ብሶት ባወራጎኋችሁ ግን የከፋብን ይቅደም ነው ነገሩ እንደ ማግማ እሳት በውስጤ እየተንተከተከ ያለው ጉዳይ ትንቢታዊ ጋብቻ የሚለውን ሃሳብ ነው ለምን ብትሉኝ ከያዝነው የለቀቅነው፣ካተረፍነው ያከሰርነው፤ብቻ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ "መሆን ከጀመረ ሰንበት በት ብሏል። ለምን አንጠይቅማ! ከዚህ ዉጥንቅጥ ወጥተን እንጠይቅ? እንጠያዬቅ አብረንም እንጠይቀው? በውኑ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በነብይ ቃል ትዳር የመሠረተ አለ? ጋብቻ እና ትንቢት ምን አገናኛቸው? ሰው ለማግባት ወዳጁን ለመወዳጀት ትንቢት መሻት ያስፈልጋል?መገለጥ አገኘን ብለው ወደ ትዳር የገቡ ሰወች በራሳቸው ውሳኔ ከተጣመሩት ያላቸው ብልጫ ምንድን ነው? መልስ ያስፈልገዋል ።

በቅድሚያ ትንቢት ማለት ምን ማለት ነው? የማለውን በወፍ በረር እንየው እስኪ :- ትንቢት{ prophecy} ከሰው ውስንነት በላይ በልዕለ ተፈጥሮአዊ ሃይል ሰው የማያውቀው ያልኖረውን ነገን ወይም ዘላለምን አሁን ባለበት ጊዜ ለሰሚው ሲገለጥ እና በዘመኑ ተፈፃሚነት ሲያገኝ ትንቢት ይባላል ፤እንዲሁም ትንቢት ማለት: እግዚአብሔር ለሰው ሊያደርገው ያሰበው አላማ ሆኖ ሰው ግን ፈፅሞ ሊያስበው የማይችለው ጉዳይ ነው። በዚህ ስጦታ በዋናነት በአዲስ ኪዳን ቤተክርስትያን አማኞች ይገለገሉበታል፤ የሚገለጠው ሰዎች በተለያዩ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ ለማፅናት፣ለማነፅ፣ተግሳፅ ለመስጠት፣ምክርን ፣ግልፅ ባል ሆነ ጉዳይ ምሪት ለመቀበል ;የዘመኑን ሃሳብ ለመረዳት በተለያዬ መንገድ ስጦታው በአላቸው ሰዎች የሚገለጥ አንዱ የፀጋ ስጦታ ነው፤ይህ ስጦታ አንድም በሰው ፈቃድ አልመጣም አይመጣም [1ቆሮ14:3:1ተሰ5:20-21:2ጴጥ1:21 ]።

" እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር " ይሻላል እና የእግዚአብሔር ቃል ሰው እንዴት ምድራዊ ህይወቱን መምራት እንዳለበት ግልፅ ለማድረግ የተሰጠ መመሪያ አለ እሱ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል? ትንቢት ሰምቶ ጋብቻ የመሠረተ ሰው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለን? መልሱ አወ አለ! ማነው የሚል ጥያቄ ካነሳችሁ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ብናነብ ትንቢት የሰማ አንድ ሰው አለን !ያውም በነብይ በህልም ሳይሆን ቀጥታ ከሁሉን ቻይ ድምፅ ሰምቶ ዋናውን የተቀበለ እርሱ ተኝቶ፣በፀጥታ ውስጥ በዝምታ፣ሃሳብ ሳያወጣ ሳያወርድ፣ሳያስመክር ሳይመክር የሰማው ኣዳም እድለኛ ነበር።ምክንያቱም እርሱ ያላሰበው በገሃድ አለም ያልተገለጠ ስለነበር ለአዳም ትንቢቱ ነበር። ፈጣሪ የፈጠረውን ሰው ምሉዕ ለማድረግ፤ በፀጥታ ውስጥ እንዲገባ ከባድ እንቅልፍ ጣለበት ምን አልባት ከእንቅልፉ ቢነቃ ፈጣሪው በሚሰራው ስራ እየገባ እንደዚህ አድርገህ ስራት እንዴ ጌታ ሆይ ምነው አፍንጫዋን እንዲህ አስረዘምከው!? ደግሞ ቁመቷ ትንሽ ከእኔ አጠር ትበል እያለ የእግዚአብሔር ስራ ሊያቃልል ይችል ይሆናል ለዚህም ነው

ከከባዱ እንቅልፍ ከጎኑ አጥንት ወጥታ ሰው እስክትሆን ድረስ ሊነቃ ያልተፈለገበት ምክንያት ( ዘፍ 2፥21-22:ኢሳ40:13) ። በዝምታ እያለ ትንቢት ሰማ የሚሆን ያልሆነ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ወደ እርሱ አመጣት አዳምም አለ። "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ስጋም ከስጋዬ ናት ሴት ትባል "[ዘፍ 2፥23] ተቀበላት ምርጫም አማራጫም የሌላት ሆና ተገኝታለች እና ወሰዳት ፣ ወደዳት ነገር ግን አዳም ምንም አይነት ጥርጣሬ እና ግራ መጋባት ለምን አልታየበትም? ለምን እንደዘመኑ ሰው ከጎኑ ያለችን ልዕልት ትቶ 'የእኔ ሌላ ናት' በሚል ብሂል አይኑ ባህር ማዶ አልማተረም? ወይስ አዳም ምንም የማያውቅ ሰው ነበር?

ተሰጠው ፣ ተቀበለ ምን መሆኗን አምኖ ? ሴት መሆኗን፣የህያዋን እናት፣ለእርሱ ተስማሚ ረዳት፣በውስጡ ላለ ስሜት ትክክለኛ መልስ እንዳላት ፣የሚወደውን እርሱን የተካፈለ ስብዕና እንደተሰጣት ተረዳ አንጅ ሸሮ በርበሬ ላይ እንዴት ናት? ፀባይ አላት ፣ ጎሳዋ ከየት መጣ ? እያሉ የተሰራ ያለቀለት አንድ እንደሚመኙት ጊዜ አላጠፋም በውንድ ወስጥ ያለ ሴትን የመቀበል አቅም ማሳያ የሆነ ህይወት ነው የኖረ እንጅ። በዚህ መርህ መሠረት የሰው ልጅ እንዲኖር ትዕዛዝ ተሰጥቷል፤ ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ።[ዘፍ2፥24:ማቴ19:6 ] በዚህ እውነት ሰዎች ትዳር ሲመሠርቱ የትውልድ ሰንሰለቱ ሲቀጥል ይስተዋላል ይህም በባህላዊ;ሃይማንታዊ መንገዶችን እየተከተለ ይፈፀማል። ይህ አልጠፋንም! ዳሩ ግን ሁሉንም ወንድ ለሁለም ሴት በአምላክ አጠቃላይ ፈቃድ የገለፀው ቢሆንም ማን ለማን? የሚል እንቆቅልሽ ዛሬም ብዙወችን ይጠይቃሉ። በእግዚአብሔር ውስጥ ሆኖ የእርሱን ( ዩሐ 1፥3:ኤር32፥19 )መፈለግን።

ለምሳሌ አንድ ባህር ጠላቂ ወደባህር ውስጥ ጠልቆ ቢገባ እርሱ ውሃው በየትኛው ሰውነቱ ክፍል እንደነካው መግለፅ ይችላል? ሁለንተናው አልተሸፈነም? በየትኛውም መንገድ ቢንቀሳቀስ በዉሃ አለመነካት ይችላል! ? ካለበት መሸፈን ከውሃው ከወጣ ብቻ ሊያመልጥ ይችላል ይህ ምሳሌ እኛን በእግዚአብሔር ሙላት ውስጥ ያለን ህይወት ይወክላል ከእርሱ ጋር ሆነን የእርሱ ያልሆነ ያገኘን ? እከሊትን እንዳገባ ጌታ ተናግሮኛል ፣በህልም አይቻለሁ፣ሳያት ደንግጬለሁ ፣ነብያት ነግረውኛል ስለዚህ በእርግጥ {ለኔ የተዘጋጀች ናት እሷ እኔም ለሷ ሆነን ነው የተፈጠርን} ከዚህ ውጭ መንገድ የለም ብለው ነገራቸው ከፋፍለው በሬ ሳያርዱ ቅርጫ እንደመጠበቅ ሆኖባቸው ድርሻቸውን እየጠበቁ የተቀመጡ ብዙወች ናቸው።

በዚህ እኛ አማኞች ባለማወቅ ተመላልሰናል ፤ ባሉን ማህበራዊ ህይወት እድሎችን (chance,possibility, fate) ይዞ ሲመጣ ያመከኑ፣በኣባይ ነብያት ያንቾው ሩቅ ሀገር ነው ጠብቂው/ቃት እየተባለ የማይፈፀም ህልም አላሚወች ሆነው የተሰነካከልሉ ;እንዲሁም መልካም የሚባል የፍቅር ህይወት እየኖሩ የነበሩ ሰወች መድረክ በለመዱ ተኩላወች እግዚአብሔር የለሁበትም በግንኙነታችሁ ፣ሞት አለበት ውጣ /ጪ !በሚል ማስፈራሪያ ብዙ የደከሙለት ፍቅር የፈረሰባቸው እንዲህ በቀላሉ ተናግረንላቸው የሚያልቅ አይደለም ሆድ ይቻለው እንጅ ።ይህ ሁሉ ሲሆን የቤተክርስትያን ምሁራን ድምፅ ለምን አልተሰማም ?የሚለውን ጥያቄ ለነሱ እንተወው ቃሉ ስለ ጋብቻ ላይ ያለው አቋም ከሌላው የህይወታችን ክፍል ተለይቶ የሚታይ ነው የሚል ትምህርት የለውም፤ ሰው በአራት አካላት ከበባ{ bound ,enshrined}ወይም ቅጥር እንዲኖር ሆኖ የተፈጠረ ነው።
እግዚአብሔር፣ነቢራዊ ተፈጥሮ፣መናፍስት እና በመጨረሻ በራሱ ተፅእኖ ውስጥ ይመላለሳል በነዚህ ሃይላት አወንታዊ እና አሉታዊ ጎን በህይወቱ ድርሻቸው ይወጣሉ።

ሰው ህይወቱን ለማስቀጠል በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ በራሱ ነፃ ፈቃድ ያልተገደበ መብት ቢኖረውም በምድር ህይወቱ ያሰበውን ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ሊያደርግ አይቻለውም ምክንያቱም በጊዜ ሃይል ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ወድቋል ካለው ጊዜና ካመጣው ነገር ጋር የማያቋርጥ ፍጭት ያደርጋል [መክ 3፥1-8]።በዚህ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር በጊዜውም ካለጊዜውም በህይወቱ ውስጥ ጣልቃ እየገባ የማስተካከል ሥራ ይሰራል [ዘፍ2፥1-3:ሚልክ3፥6 :]ሰይጣን ደግሞ ከጊዜ በታች የሆነው *ከጊዜ በታች እንደሆነ ማሳያው የፍርድን ቀን እርሱም እየተጠባበቀ መሆኑ ይገልፃል ስለዚህ በሰው ድክመት እየተጠቀመ ሰውም እግዚአብሔርም የደከሙለትን ህይወት ማበላሸት ስራ ይሰራል።

እንዲሁም ተፈጥሮ{nature as original } የበለጠ በአካባቢያዊ ተፅእኖ{ environment with time influence } አማካኝነት ፍላጎቱን ፤ ይህ ማለት አንድ ሰው አዲስ አበባ ተወልዶ ቢያድግ ከአዲስ አበባ ሰወች ጋር በሚኖረው ግንኙነት በዙሪያው ካሉ ቆነጃጅት የማግባት ያልተገደበ አቅም አለው ይህው ሰው ባህር አቋርጦ ኬንያ ሄዶ መኖር ቢጀምር አሁንም ከፈለጋት ኬኒያዊትን እመቤት ጋር ይጣበቃል ፤ ይህ አንድ ሰው ለአንድ ነው የተፈጠረ ብለው ለሚያስቡ አካላት መልስ ይሆናል እነዚህ ሰወች ያልተረዱት። እውነት በሰው ልጅ ግንኙነት{ social interaction } ውስጥ ተፈጥሮ ያላትን ድርሻ እና ከእኛው ጋር አንዳንዴ ተስማምታ ሌላ ጊዜ በጫና የምታሳድረውን ተፅእኖ ቆም ብለው ሊያስተውሉ አልቻሉም። በማሰብ አርነት እንውጣ? በእግዚአብሔር ቃል በትንቢት ያገባ ሰው ከኣዳም ውጭ ከሌለ ፤የምናውቀው በራሳችን በተሰጠን የማመዛዘን የመለዬት መንፈስ፤[ ዘዳ30: 19:ሚክ6:8:ኢሳ15:9:2ጴጥ1:2-3፡ ሮሜ12:2 1ቆሮ2:11-
16:1ዩሐ2::20-21 :27]

ወይም ደመ ነፍስ እና ህሊና፤የተፈጥሮ ህግ የምንወደውን ሰው መርጠን የማግባት መብት ካለን "፤ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔእግዚአብሔ ነውና። " (ፊል 2:13:1ቆሮ7:36-39 ] "የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል" እንዲሁም በጌታ ይሁን እንጅ የወደቸውን እንድታገባ ተፈቅዶላታል "ካለ ስለምን ትንቢታዊነት ተጠናወተን?

እስቲ በነብይ ቃል አገባን ያሉ ሰወችን ህይወት እና ያለውን የፍቅር ሀያልነት አምነው በየዋህነት ወደ ትዳር የገቡ ሰወችን ህይወት እንይ ምኑ ጋር ነው የተሻለ? ምንም አይነት ግላዊ ጥረት የሌለበት ህይወት የመሩት? እግዚአብሔር የፈቀደው ነው ብለው ጌታ ተናግሮኛል በሚል ነገሮችን
ሳይመረምሩ በሩጫ ወደ ትዳር የገቡ ሰወች እና ከጊዜያት በኋላ አስከፊ ችግር ውስጥ የገቡ ሰወች ታሪክ የለምን? ጌታ ፍፁም ነው ታዲያ ለምን መልካም ትዳርን አጡ? ብዙ ክርስትያኖች ኮምፓስ እንደሌላት መርከብ አቅጣጫቸው ጠፍቶባቸዋል። አብዛኛው ህይወታችን ፍርሃት አለመታመን ብቸኝነት ውስጥ ስለሚሆን በደካማነታችን የሚገለጥ የሽንፈታችን ማሳያ መሆን ከጀመረ ቆይቷል።

ስማኝ እወነቱን ልንገርህ አንተ የወደድካት ከእግዚአብሔር ያልወደድካት ከዲያብሎስ አድርገህ ካሰብክ በአለም ካሉ ምስኪኖች አንዱ ነህ ማለት ነው። ለምን አትልም ያች የጠላሃት የሰይጣን ሃሳብ ነበር እና ጌታ ለአንተ መልካሙን ሰጥቶ ለሌላኛው ባለንጀራህ ደግሞ አንተ በፀሎትህ ብዛት ከሰይጣን እንደሆነች የደረስክባት ሴት ለእርሱስ ምን ልትሆን ነው! ? ነው ወይስ ሰይጣን ከሰው ሰው ይለያያል ለኔ ሰይጣን ለሌላው መላዕክ ነው እንዳትል አደራህን ትስታለህ። በአጠቃላይ በውስጥህ የጌታ መንፈስ አለ ሁሉን የሚችል አምላክ ማስተዋልን በአንተ ውስጥ ነው፤ ራስህን ጠይቅ ;መልስ የሚሰጥህ ነገር አዋቂ፣ወይም በሆነ አጋጣሚ ያነበብከው መጣጥፍ ሳይሆን ፍቅር ነው ።"፤ ነገር ግን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፥ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጣል። ( እዩ32፥8፡መዝ36፥9 ኢሳ58፥11) ፍቅር ከሁሉ ይልቃል ሁሉ ያልፋል እርሱ ግን አያልፍም ሰለሆነም ፍቅር አይመቀኝምና ጠይቀው ነገሮችን እና አካሄዳቸውን ግልፅ ያደርግልሃል በአጠቃላይ በትዳር ውስጥ ትንቢት መሻት በሁለት ነገሮች እምነት እንደሌለህ ያሳያል።

የመጀመሪያው የነገሮች ሁሉ ጀማሪ በሆነው ፈጣሪ አለመታመን ሲሆን በሁለተኛነት በራስ እርግጠኛ አለመሆንን ያሳያል ትዳር ወስጥ ፍቅር አለ ፍቅር ማለት ደግሞ በሚለዋወጥ ሁኔታ ውስጥ መጀመሪያ ያ የነበረንን ስሜት እስከ መጨረሻው የማስቀጠል አቅምን ማግኘት እንጂ ሌላ እንዳልሆነ እንረዳለን። ሰለዚህ በፍፁም
ፍቅር ፍርሃትን እናሸንፈው ( 1ቆሮ13:8:1ዩሐ4 :18) መፅሐፉም ብዙ ምክር ባለበት ጥፋት በዚያ አለ ይላልና ይህን ሰውን ስራ የማስፈታት ፍልስፍና ነፃ ወጥተን በራሳችን የፍቅር ቤታችንን እንስራ...

<ተጨማሪ ማብራሪያ ጥቅሶች (መክ3:11 ምሳ5፥21 ምሳ20፥24:21 ሐዋ10:19 ሐዋ11:28 (13:2) (16:7) (20:23) 1ዩሐ 4:1 ምሳ30:18-19 ምሳ11 ኤር 29:11 መዝ37:4-6 መዝ36:9 መዝ33:11 1ጢሞ5:16 ዘፍ24:67 ዘፍ28:1-2 )

# ቃልኛ ምርጫ

## መሰማት ያለባቸው 2 የተመረጡ አልበሞች




**የአልበም ስም** :- እግዚአብሔር ትልቅ
ዘማሪት :- ህሊና ካሳሁን
**አልበሙ የወጣበት አመት** :- 2007ዓ.ም
የተመረጠ ቁጥር :- Track 9 ( ይገርመኛል )

AVAILABLE ON SPOTIFY




**የአልበም ስም** :- እለምንሀለሁ
ዘማሪት :- ሀምሌት በልጁን
**አልበሙ የወጣበት አመት** :- 2011ዓ.ም
የተመረጠ ቁጥር :- Track 13 ( እንዳንተ መሀሪ )

AVAILABLE ON YOUTUBE

## በዚህ እትም

እነዚህን አልበሞች በመስማት እንድትባረኩ ጋብዘናችኋል!

# አምደኞቻችን
## AUTHORS







ነብይ መሳይ አለማየሁ | ዘሪሁን ግርማ | ቢኒያም አዲሱ | አቤኔዘር አለማየሁ | አድነው ተመስገን




# መፅሔታችንን ስላነበቡ
# እናመሰግናለን

**ቃልኛ ዲጂታል መንፈሳዊ መፅሔት**

በቃልቲዩብ ተዘጋጅቶ በ MHgraphics የተሰራ

**SEARCH @KALTUBE**

ለቀጣይ እትሞች ብሎም እለታዊ መንፈሳዊ ዝግጅቶቻችንን ለመከታተል
በማህበራዊ ትስስር ገፆቻችን ይከተሉን።